

# ትንሣኤ



የዞር አባ ጽርሐ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ይህችን ትመስላለች


www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ። »

ዋና አዘጋጅ ቀ. ልሣነ ወርቅ በዛብህ
ም/ አዘጋጅ መ/ ክኅሬ. ርግብ ማርቆስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤

# ማውጫ

## አርእስት

ገጽ

ደብዳቤዎች ........ ፩
ይህንን አድርገ ያንንም አትተው ርእስ አንቀጽ ........ ፪
የናዝሬት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በቅዱስነታቸው ተባርኮ ታቦቱ ገባ ........ ፬
የሃይማኖት ዓምድ ........ ፯
ስለትዳሚና አውድ አከባበር ........ ፰
የቤተ ክርስቲያን አመሠራረት ........ ፲
ልማት በቤተክርስቲያን ........ ፲፩
ማብረ ኖሎት ........ ፲፪
ዜና ሊቃውንት የስመ ጥሩው የመሪጌታ ጌታሁን ዓይኔ አጭር የሕይወት ታሪክ ........ ፲፫
የቅድስት ሐና ቤተክርስቲያን ታሪክ በአጭሩ ........ ፲፬
የጤና ዓምድ ........ ፲፯
ዜና ዕረፍት ........ ፲፰
ስብከተ ወንጌል (ክፍል ፲፩) ........ ፲፱
በጠ ቤተ ክህነት ለሰባኪያን ወንጌል ኮርስ ተደረገ ........ ፳፩
የዙር አባ አረጋዊ ገዳም ታሪክ በአጭሩ ........ ፳፪
ዜና ሊቃውንት ሊቀ ጠበብት ሐውዩን ........ ፳፬

# ደብዳቤዎች

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡
ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በቅድሚያ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ፡ ከሰላምታዬ ቀጥዬ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አቀርባለሁና ተገቢውን መልስ እንደምትሰጡኝ ተስፋ አደርጋለሁ ።

፩ኛ በሀገራችን በኢትዮጵያ ከእስልምናና ከክርስትና እምነት የትኛው ነው ቅድሚያ ያለው ?

፪ኛ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የተሠራችው የት ነው? በስንተኛውስ ክፍለ ዘመን ነው ?

፫ኛ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ቀሳውስትና ዲያቆናት ምን ምን ነገሮችን ማወቅና? ምን መሆን አለባቸው?

፬ኛ ከቤተ ክርስቲያን ጉልላት ላይ ያለው የሰጐን እንቁላል ምን ምክንያት እንዳለው ብትገልጹልኝ?

፭ኛ የደብር አስተዳዳሪ (አለቃ) በየቦታው እየዞረ ማስተማር ይገባዋል ። ወይስ በዚያው በሚያስተዳድረው ደብር ብቻ ተወስኖ ማስተማር አለበት?

ዲያቆን ተስፋዬ ብርሃኑ
ሻሸመኔ
ሸዋ ሀ/ስብከት

መልስ ዲያቆን ተስፋዬ ብርሃኑ ስላቀረብክልን ሰላምታ እኛም በበኩላችን መንፈሳዊ ሰላምታ በመስጠት ላቀረብካቸው ጥያቄዎች መልስ እንሰጣለን ።

የመጀመሪያ ጥያቄህ በሀገራችን በኢትዮጵያ ከክርስትና እምነትና ከእስልምና እምነት የትኛው ይቀድማል የሚል ነው መልሱም የክርስትና እምነት ይቀድማል ነው ። ይኸውም የክርስትና እምነት የተሰበከው ከክርስቶስ ልደት ወዲህ በ፴፬ ዓመት በኢትዮጵያ ዊው ጃን ደረባ ነው ። ያን ጊዜ በሀገራችን የእስልምና ሃይማኖት እንዳልነበር ከታሪክ እንረዳለን የእስልምና ሃይማኖት ወደ ሀገራችን ገባ የሚባለው በ፯ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሲሆን የሃይማኖቱም መሥራች ተነሣ የሚባለው በ፮ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው ይህንንም ታሪክ በሰፊው ለመረዳት ፡ በሊቀ ጠበብት አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ የተደረሰውን መጽሐተ አሚን የተባለውን መጽሐፍ ገጽ ፴፪ ላይ ተመልከት ።

ለ፪ኛ ጥያቄህ መልሱ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የታነፀችው በ፶፪ ዓ/ም ሲሆን ቦታውም በመካከለኛው ምሥራቅ በምትገኘው በፊልጵስዩስ ነው ፡

ሦስተኛው ጥያቄ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ቀሳውስትና ዲያቆናት ምን ምን ማወቅና ምን መሆን እንዳለባቸው ግለጹልኝ የሚል ነው።

የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ቀሳውስትና ዲያቆናት ምን ምን ማወቅና ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሐዋርያው ጳውሎስ ለደቀ መዝሙሩ ጢሞቴዎስ ሲገልጽ ፡ ኤጲስ ቆጶስ (ቄስ) እንዲህ ሊሆን ይገባዋል ፡ የማይነቀፍ የአንዲት ሚስት ባል ልከኛ ራሱን የሚገዛ እንደሚገባው የሚሠራ እንግዳ ተቀባይ ለማስተማር የሚበቃ የማይሰክር የማይጨቃጨቅ ገር የሆነ የማይከራከር ገንዘብን የማይወድ ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር በማለት ስለቄሱ ይናገርና ወደ ዲያቆናቱ መለስ በማለት ፡ እንዲሁም ዲያቆናት ጭምቶች በሁለት ቃል የማይናገሩ ፡ ለብዙ ወይን ጠጅ የማይጎመጁ ነውረኛ ረብ የማይወዱ በንጹሕ ሕሊና የሃይማኖትን ምሥጢር የሚይዙ ሊሆኑ ይገባቸዋል ። እንደዚህም ደግሞ አስቀድመው ይፈተኑ ከዚያም በኋላ ያለ ነቀፋ በዲቁና ሥራ ያገልግሉ ብሏል።

፩ኛ. ጢሞቴዎስ ፫፡፪-፯፡ ፰-፲ ተመልከት ከዚህ ሌላ ማስረጃ የሚያስፈልግ አይመስለንምና ይኸው ይበቃል ።

፬ኛ በቤተ ክርስቲያን ጉልላት ላይ ስለሚሰካው የሰጐን ዕንቁላል ምሥጢር ጠይቀሃል ፡ ሰጐን እንቁላል ከጣለችበት ቀን ጀምሮ ጫጩት እስከምትቀፈቅፍ ድረስ ከእንቁላሏ አትለይም ምግብ ለመፈለግ በምትሄድበት ጊዜ እንኳን ተባቱን ተክታ ነው የምትሄደው

ወደ ገጽ ፬ ይዞራል



www.ethiopianorthodox.org

ርእሰ አንቀጽ

# ዘንተ ግበሩ ወዝክተኒ ኢትኅድጉ
# ይህንን አድርጉ ያንንም አትተው
## ማቴ ፳፫.፳፫

በዘመነ ኦሪት አሥራት በኩራት ቀዳማይያት ለእግዚአብሔር አገልጋዮችና ለቤተ መቅደሱ መገልገያ መክፈል የተለመደ መንፈሳዊ ግዴታ ነበር አሥራት ማለተ ወጥቶ ወርዶ ነዶ በርዶ ጉልበትን አድክሞ ወዝን አንጠፍጥፎ ካገኙት ገንዘብ ከአሥር አንደኛውን ክፍሉ መስጠት ሲሆን በኩራት ደግሞ እያረቡ ከሚጠቀሙባቸው እንስሳት ላምም ሆነ በግ ፍየልም ሆነ ሌሎች እንስሶች ሲወልዱ በመጀመሪያ የተወለደውን ለቤተ እግዚአብሔር አገልግሎት እንዲውል መስጠት ነው እንዲሁም ቀዳማይያት የሚባለው ከአዝርዕትም ሆነ ከአትክልት አስቀድሞ ለመብል የደረሰውን ቀርጦና አጭዶ ወስዶ ለቤተ እግዚአብሔር አገልጋዮች ሌዋውያን ካህናት መስጠት ነው ፡ ይህንንም እግዚአብሔር ለሙሴ ሲናገር ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው በላቸውም ወደምሰጣችሁ ምድር በገባችሁ ጊዜ እህሏንም ባጨዳችሁ ጊዜ በፊት ያጨዳችሁትን ነዶ ወደ ካህን አምጡ ነዶውንም ባቀረባችሁ ቀን ነውር የሌለበት ጠቦት አንድ ዓመት የሆነው ለሚቃጠል መሥዋዕት ለእግዚአብሔር አቅርቡ የእህልም ቁርባን ከአሥር አንድ ብሎታል ኦሪ ዘሌ ፳፫.፲ ፡

በእግዚአብሔር ስም አምነው በሕገ ጸንተው የእርሱን ትእዛዝ ተቀብለውና ጠብቀው የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ከላይ የተጠቀሱትን የመፈጸም ግዴታ ነበረባቸው ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች በኦሪቱ የታዘዘውን አትድለው የተገኙ እንደሆነ ያረቡት እንስሳ የዘሩት ዘር የተከሉት ተክል አይባረክላቸውም ነበር እህሉን ዋግ ይመታዋል ከብቱን ተኩር ይፈጀዋል አሥራቱንና በኩራቱን ቀዳማይያቱን በወቀቱ ሲከፍሉ ግን እግዚአብሔር አምላክ በሀብት ላይ ሀብትንበየጊዜው ይጨምራላቸው እንደነበር ከቅዱስ መጽሐፍ እንረዳለን ይህንንም ትእዛዝ እግዚአብሔር አምላክ የእስራኤላውያን መሪ ለነበረው ሙሴ ሲናገር "ከእርሻው በየዓመቱ ከምታገኘው ከዘርህ ፍሬ ሁሉ አሥራት ታወጣለህ ሁልጊዜ አምላክህን እግዚአብሔርን መፍራት ትማር ዘንድ ስሙ እንዲጠራበት በመረጠው ስፍራ በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት የእህልን ፡ የወይን ጠጅህንም የዘይትህንም አሥራት ፡ የላምህንና የበግህንም በኩራት ብላ ፤ አምላክህ እግዚአብሔር በባረከህ ጊዜ መንገዱ ሩቅ ቢሆንም እንስሳውን ሽጠህ ገንዘቡን ወስደህ መሥዋዕት ከሚቀርብበት አካባቢ ገዝተህ ለአምላክህ አቅርብ ፡ የአዝመራህንም ፍሬ አሥራት ሁሉ አምጥተህ ስጥ በምታደርገው በእጅህ ሥራ ሁሉ እግዚአብሔር ይባርክህ ዘንድ ነው ።

እንዲሁም ላምህና በግህ የወለዱትን ተባት የሆነውን በኩራት ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ትቀድሳለህ በበሬህ በኩራት አትሥራበት የበግህንም በኩራት አትሸልት በአምላክህ እግዚአብሔር ፊት ብሏቸው ብሏል ኦሪት ዘሌ. ፲፫ ፳፬-፳፱, ፲፭, ፲፱ ፡

አብረሃም የወንድሙ ሎጥን ጠላቶች ነገሥተ ኮሎ ዶጎምርን ወግቶ አሸንፎ ከብቱንም ሁሉ ካስመለሰ በኋላ መልከ ጼድቅ እንጀራና የወይን ጠጅን አመጣ እርሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበር አብርሃም ሰማይንና ምድርን ለሚገዛ ለልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ነው ጠላቶችህን በእጅህ የጣለልህ ልዑል እግዚአብሔርም የተባረከ ነው በማለት ባረከው በዚያን ጊዜ አብርሃም ካለው ገንዘብ ሁሉ ከአሥር አንድ አውጥቶ ለመልከ ጼዴቅ ሰጥቶታል ዘፍ. ፲፬.፲፯-፳

ይህንንም ሊቃውንት ወይዘመነ ሐዲስ አምጥተው ሲተረጉሙ አብርሃም የምእመናን መልከ ጼዴቅ የቀሳውስት እንጀራና የወይን ጠጅ የሥጋና የደሙ ምሳሌ ነው ብለዋል

በእርግጥ አሁንም ቢሆን የቀሳውስት ተግባር ምእመናንን መባረክ ፡ መቀደስ ማንጻት ሥጋውንና ደሙን ከኃጢአት ለነፃ ማቀበል ያልነጹት እንዲነጹ ያልተዘጋጁት እንዲዘጋጁ መምከርና ማስተማር ሲሆን ምእመናን ደግሞ ከወጡበት ከወረዱበት ከደከሙበት ገንዘባቸው እንደ አብርሃም ከአሥር አንድ አውጥተው ለቤተ ክርስቲያን መስጠት ይገባቸዋል ፡ በመጀመሪያ እንደተገለጸው ጌታችን መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ይህንን አድርጉ ያንንም አትተው ያለውም በኦሪቱ የታዘዘውን መፈጸም መሆኑንና ከዚያም አብልጠ ለእግዚአብሔር መክፈል በክብር ላይ ክብርን የሚያሰጥ መሆኑን ሲያስረዳ ነው ።

ጌታችን ሲያስተምር ስጡ ይሰጣችኋል በሰፈራችሁበትም ይሠፈርላችኋል ብሏል አባቶችም መስጠት ቤት አይፈታም ይላሉ ቅዱስ መጽሐፍም ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ንዑድ ክቡር ነው ይላል የሐ ሥራ ፳.፴፭ የሰው ሁለተናው ሰውነቱም ገንዘቡም የእግዚአብሔር ነው ለእግዚአብሔር ብሎ የሚሰጠው ስጦታ የሚፈጽመው በጎ አድራጎት ሁሉ ከፈጣሪ ጋር የሚያገናኝ ነው መንገድ ደንጊያው ተፈንቅሎ እሾሁ ተነቅሎ የተደለደለ እንደሆነ በቀንም በሌሊትም ቢሄዱበት እንቅፋት እንደሌለው ሃይማኖቱ የጸናና ምግባሩ ያማረ ሰውም በምድራዊ ኑሮው በሥጋው ፡ በሰማያዊ ዓለም በነፍሱ ጉዳት አያገኘውም መሰናክልም አይገጥመውም ።

ስለዚህ በቅዱሳት መጻሕፍት የታዘዙትን ሕግጋት ለመፈጸም ባለን አቅም ሁሉ መጣር ይኖርብናል የእግዚአብሔር ሕግ የሚከብደው ላላደረገውም ለሚል ሰነፍ ሰው ነው እንጅ አደርገዋለሁ ለሚል ከባድ አይደለም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና ለነፍሳችሁ ዕረፍት ታገኛላችሁ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀላል ነው ብሎ ተናግሯልና።

## ዜና ሊቃውንት

ከገጽ ፳፱ የዞረ

የሄዱ ሰው ናቸው ።

ሊቀ ጠበብት ሐረገ ወይን ደምሴ በሕይወት ዘመናቸው ፫ ሴቶችና ፬ ወንዶች ልጆች አፍርተ ዋል ምንም ደግና ባለሙያ ቢሆኑ ከሞተ ሥጋ የሚቀር የለምና በተ ወለዱ በ54 ዓመታቸው ነሐሴ ፪ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ።

በዚች በክርስቶስ ደም በተቀደሰች ቤተ ክርስቲያን ሥጋቸውን በክብር ለማሳረፍ የተሰበሰበን ዘመዶቻቸው ፡ የሃይማኖት አባቶ ቻቸውና ጓደኞቻቸው እግዚአብ ሔር ነፍሳቸውን በክብር እንዲቀ በላት ለቤተ ሰቦቻቸውም የሚያጽ ናና ቅዱስ መንፈስን አምላካችን እንዲልክላቸው እየለመንን ለመ ጨረሻ ጊዜ እንሰናበታቸዋለን ።

ዘመዶቻቸው

www.ethiopianorthodox.org

# የናዝሬት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ ፓትርያርኩ ተባርኮ ታቦቱ ገባ

በሸዋ ሀ ስብከት በኤረርና ከረዩ አውራጃ ናዝሬት ከተማ የምትገኘው የቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ሕንፃ ሥራ ተፈጽሞ ታቦቱ ከመቃኞው ወጥቶ አዲስ ወደ ተሠራው ቤተ ክርስቲያን የገባው መስከረም ፳ ቀን ፲፱፻፹ ዓ ም ነው ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ብፁዕ አቡነ ገሪማን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰዳን ሊቀ ጳጳስና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ተጠባባቂ ዋና ጸሐፊን ፣ ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕን የመንፈሳዊ ፍርድ ቤት ሊቀ ጳጳስን ፣ መጋቤ ካህናት አማን ዘወልዴንና ፣ ሌሎችንም የክብር ተከታዮቻቸውን አስከትለው መስከረም ፲፱ ቀን ፲፱፻፹ ዓ ም ከሰዓት በኋላ በ፱ ሰዓት ከሩብ ጉዟቸውን ወደናዝሬት ቀጥለዋል ፣ ለ፲፩ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሲሆን ናዝሬት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ሲደርሱ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሀ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ፣ ዶ. ደርቤ ወ ጻድቅ የሀ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ፣ ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ካህናት የሰንበት ት ቤት ተማሮች በርካት ያሉ ምእመናንና ምእመናት በመዝሙርና በእልልታ በጭብጨባ ተቀብለዋቸዋል ።

የሰንበት ተማሮችም እቅፍ አበባ አበርክተውላቸዋል ቅዱስነታቸው ለመቀበል የተሰለፉትን ምእመናን እየባረኩ ወደ ውስጥ ገብተው ጸሎት ከጸለዩ በኋላ የቡራኬው ጸሎት ተጀምሯል ውሀው በማህን ቀርቦ ቅባ ቅዱስ ተጨ



ቅዱስነታቸው መንፈሳዊ መመሪያ ሲሰጡ

ምሮ ከተጸለየበት በኋላ የወይራና የወይን ቅጠል በአንድ ላይ በማጃ እራፊ ታሥሮ ቅዱስነታቸው በዚያ ከውሀው እየነከሩ አዲስ የተሠራውን ሕንፃ በውስጥም በውጭም እየተዘዋወሩ ሲቀቡ በአራቱ ማዕዘን ምስባክ እየተሰበከ ወንጌል እየተነበበ አቡን እየተመራ አንድ ጊዜ ዑደት ተደርጓል ፣ ፲፩ ሰዓት ተኩል ሲሆን የቡራኬና የመርጨቱ እንዲሁም የመቀባቱ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞ ቅዱስነታቸው ከክብር ተከታዮቻቸው ጋር በመሆን ለዕረፍት ወደ ተዘጋጀላቸው ቦታ ሄደዋል ።

መስከረም ፳ ቀን ፲፱፻፹ ዓ ም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ከጧቱ ፲፪ ሰዓት ከ፴ ደቂቃ ከቤተ ክርስቲያን ሲደርሱ ልብሰ ተክህኖ የለበሱ ካህናት የሰንበት ተማሮች በመዝሙር ተቀብለዋቸዋል ቅዱስነታቸው ለ፴ ደቂቃ ያህል ጸሎት እንዳደረጉ ጸሎተ ቅዳሴው ተጀምሯል ጸሎተ ቅዳሴውም የተመራው በቅዱስነታቸውና በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ነበር ፣ በቅዳሴውም መጨረሻ ቅዱስነታቸው ጸሎተ ቡራኬ ሲያደርጉ የዚህ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ሥራ ከተጀመረ ፰ ዓመት ሆኖታል ብዙ ገንዘብ ወጥቶበታል ፣ ብዙ ጉልበትም ደክሞበታል ፣ ሥራው አሁንም አልተጠናቀቀም ፣ ብዙ ይቀረዋል ፣ ነገር ግን ዛሬ ጽላቱ ወደዚህ አዲስ ወደተሠራው ቤተ ክርስቲያን እንዲገባ ያደረግነው ሥራው ተጠናቋል በማለት ሳይሆን እየተቀደሰበት፡ እየተጸለየበት የቀረው ሥራ እንዲፈጸም ነው ሲሉ ተናግረዋል ።

በዚሁ ዕለት ከ፫ ሰዓት በኋላ ቅዱስነታቸው ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ከክብር ተከታዮቻቸው ጋር በመሆን በናዝሬት ከተማ የሚገኙትን የመድኃኔ ዓለምንና የቅዱስ ገብርኤልን አብያተ ክርስቲያናት ጎብኝተዋል ።

## መስከረም ፳፩ ቀን ፲፱፻፹ ዓ/ም

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ከክብር ተከታዮቻቸው ጋር በመሆን ጧት በሦስት ሰዓት ቤተ ክርስቲያን ሲደርሱ የቤተ ክርስቲያኑ የደውል ድምፅ ለ፳ ደቂቃ ያህል ከማስተጋባቱም ሌላ ካህናቱም ልብሰ ተክህኖ ለብሰው መስቀልና ጽንሐሕ ይዘው የሰንበት ት ተማሮችም እየዘመሩ ተቀብለዋቸዋል ቅዱስነታቸውም ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ገብተው ጸሎት ካደረጉ በኋላ ፬ ሰዓት ተኩል ሲሆን ታቦቱ ከመንበረ ክብሩ ወጥቶ ዑደት ተደርጓል ፣ ከዑደት በኋላ ታቦቱ በዓውደ ምሕረቱ ላይ እንደቆመ መዘምራኑ "ሃሌ ሃሌ ሉያ ለቤተ ክርስቲያን ልዑል ሐነፃ" የሚለውን ያሬዳዊ መዝሙር ለ፳ ደቂቃ ያህል አሸበሸቡ ፣ የሰንበት ት ቤት ተማሮችም መንፈሳዊ መዝሙር ዘምረዋል ፣ አቶ እሸቱ ይግዛው የቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ አሠሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ የቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ ከተጀመረ እንሥቶ እስከ ዛሬ ድረስ የተደረገውን የሥራ ይዞታ አጠቃሎ የያዘ ሪፖርት አንብበዋል ።

ቀጥሎም ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሀ ስብከት ሊቀ ጳጳስ "ጥቀ ፍቁር አብያቲከ እግዚኦ እግዚአ ኃያላን" ትርጉም የኃያላን ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ! ቤቶችህ እጅግ የተወደዱ ናቸው በሚል ርእስ ተንሥተው በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ስም የተጀመረው ቤተ ክርስቲያኗ እጅግ በሚያስደስት ሁኔታ ተፈጽሞ ስናየው እመቤታችን እንኳን ደስ አለሽ እንላታለን እንዲሁም ለዚህ ቤተ ክርስቲያን ሥራ ከገንዘባቸው አስተዋጽኦ በማድረግ በጉልበታቸው በምክራቸው አስተዋጽኦ ያደረጉትን ሁሉ እንኳን ደስ አላችሁ ብለዋል ።

ብፁዕነታቸው ዕለቱ ብዙኃን ማርያም የሚባልበትን ምክንያት ሲገልጹ

፩ኛ. በ፫፻፳፭ ዓ ም በኒቅያ የተሰበሰቡት ፫፻፲፰ ሊቃውንት በዛሬው ዕለት ሲሆን ፣ ፪ኛ. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትን ግማደ መስቀል ከኢየሩሳሌም አስመጥተው ዳግማዊ ዓጼ ዳዊት ስናር ሲደርሱ ወደመካከል ኢትዮጵያ መስቀሉን ሳያደርሱት ስለሞቱ መስቀሉም በዚያው ይኖር ነበር ልጃቸው ዓጼ ዘርአያዕቆብ ከስናር አምጥተው በግሸን አምባ ቤተ መቅደስ አሠርተው ያስቀመጡበት ነው ከዚህም የተነሣ በዓሉ በሁሉም ክርስቲያን ዘንድ ይከበራል በቅዱስነትዎ መዋዕለ ሢመት የተጀመሩት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ፍጻሜ እያገኙ ናቸው ይህም የቅዱስነትዎን ከአምላክ የተሰጥዎን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የሚያስረዳ ነው ካሉ በኋላ ይህ ቤተ ክርስቲያን የተዋህዶ ሃይማኖት የሚነገርበት ድውይ የሚፈወስበት ይሁን በማ

## ደብዳቤዎች

ከገጽ ፩ የዞረ

ተባቱን ሳትተካ የሄደች እንደሆን ግን እንቁላሉ ወደ ደንጊያነት ተለውጦ ይቀራል ፣ እንጂ ልጅ ሊሆናት አይችልም ።

ስለዚህ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት ሰጐኗን በመንፈስ ቅዱስ እንቁላሉን በምእመናን መስለው ይናገራሉ ፣ እንቁላሉ ከሰጐኗ ሲለይ ደንጊያ ሆኖ እንደሚቀር መንፈስ ቅዱስም የተለያቸው ምእመናን ለምንም አይጠቀሙም በማለት ይተረጉማሉ፡ ይህንን ምሥጢራዊ ትርጉም መሠረት በማድረግ ሊቃውንቱ የሰጐን እንቁላል የምእመናን ምሳሌ ነውና ለቤተ ክርስቲያን ጉልላት እንደጌጥ ሆኖ ይሰካ በማለት በጉልላት ላይ እንደጌጥ ይደረጋል ። ምሳሌው ግን ከላይ እንደተገለጸው የምእመናን ምሳሌ ነው ።

፫ኛ የደብር አስተዳዳሪ በየቦታው እየሄደ ማስተማር ይገባዋልን ብለህ ለጠየቅኸው መልሱ የሚሰጠው እንደ ካህኑና ቤተ ክርስቲያኑ ነው የሚያስተዳድረው ደብር ብዙ ምእመናን የማይገኙበት ከሆነ በርከት ያሉ ምእምናን ወደሚገኙበት ደብር ሄዶ ቢያስተምር ስሕተት አይደለም ግን በሚያስተዳድረው ደብር ብዙ ምዕመናን እያሉ እነርሱን ትቶ ወደሌላው ደብር ሄዶ ማስተማር አይገባውም በመጀመሪያ ደረጃ በሚያስተዳድረው ደብር የሚገኙትን ምእመናን በትምህርተ ወንጌል ማጥገብ አለበትና ።





www.ethiopianorthodox.org

ለት ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ንግግራቸውን አጠቃለዋል ።

ቀጥሎም ቅዱስነታቸው ጸሎተ ቡራኬ ሲያደርጉ ባደረጉት ንግግር ኢያዕመራ ዮሴፍ እስከ አመወለደት ወልደ ዘበኩራ "የበኩር ልጇን እስክምትወልደው ድረስ ዮሴፍ አላወቃትም የሚለውን ወንጌል ሲያብራሩ ዮሴፍ ድንግል ማርያምን አላውቃትም ማለት ጊታችንን ፀንሳ እስከ ምትወልደው ድረስ በአንድ ኅብረ መልክዕ አያውቃትም ነበር አንድ ጊዜ እንደ ጽጌረዳ ሁና ስትታየው በሌላ ጊዜ እንደሮማን አበባ ሁና ያያታል እንዲሁም እንደፀሐይ ብርሃን ሁናለማየትም የሚቸገር በት ጊዜ እንደነበር ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳናል ከወለደችው በኋላ ግን ለዮሴፍ በአንድ ኅብረ መልክዕ ስለታየችው አወቃት ማለቱ ስለዚህ ነው ብለዋል።

ቅዱስነታቸው መንፈሳዊ መልእክታቸውን በመቀጠል ቤተ ክርስቲያን ኃጢአት የሚሠረይባት ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኝባት የክርስቲያን ቤት ስለሆነች እናንተም የሠራችሁት የጋራ ቤታችሁን ነው ይህንን የመሰለ ቤተ ክርስቲያን ሠርቶ ሲያበቁ ደግሞ ብቻውን ማስቀመጥ አይገባም ካህናት የተሟሉ እንዲሆኑ ማድረግም ያስፈልጋል ካሉ በኋላ ደብሯ ደብረ ፀሐይ ቅድስት ማርያም እንድትባል ደብሯን የሚያስተዳድረው መልአከ ፀሐይ እየተባለ እንዲጠራ ደብሯን የሚያገለግሉ ሊቃውንት እንደሞያቸውና እንደ አገልግሎታቸው እየተመረጡ ሊቀ ጠበብት ፡ ርእሰ ደብር ፡ ቀኝ ጌታ እየተባሉ እንዲሾሙ ፈቅደው ምዕራገ ጸሎት ካደረጉ በኋላ ታቦቱ ወደመንበረ ክብሩ ተመልሶ ገብቶ ጸሎተ ቅዳሴው ቀጥሏል ፡ ጸሎተ ቅዳሴው በ፱ ሰዓት እንዳበቃ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ጸሎተ ቡራኬ አድርገው ሲያበቁ ሠርሐተ ሕዝብ ሆኗል ፡ ቅዱስነታቸውም ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ከክብር ተከታዮቻቸው ጋር በመሆን በ፲ ሰዓት ተኩል ከናዝሬት በሎነሚት ከምሽቱ አንድ ሰዓት ላይ ከመንበረ ፓትርያርካቸው ደርሰዋል ፡

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የመጀመርም የመሥራትም የመፈጸምም ጸጋ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ስለሆነ በመዋዕለ ሢመታቸው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ተጀምረው ፍጻሜ አግኝተዋል ፈርሰው የነበሩትም ተሠርተዋል ያረጁትም አብዛኞቹ ታድሰዋል የካህናቱ ኑሮም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ በመሔድ ላይ ይገኛል ወደፊት ያልተሠሩት አብያተ ክርስቲያናት እንዲሠሩ ያረጁት እንዲታደሱ የፈረሱት እንዲጠገኑ ለቅዱስነታቸው ረጅም ዕድሜ ከሙሉ ጤንነት ጋር እንመኝላቸዋለን ።

የዜናው አቅራቢ ቀ.ልግን ወርቅ በዛብህ

# የሃይማኖት ዓምድ

ከብፁዕ አቡነ መርሐ ክርስቶስ

**መግለጫ ፡** በዚህ ዓምድ የምናሰፍረው ጽሑፍ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትን እና ሥርዓተ ሃይማኖቱን የሚገልጽ ነው ።

**ሃይማኖት ፡ ምንድር ነው ?**

ሃይማኖት የምንለው ቃል ለዓለም ፈጣሪ አለው ብለን የምናምነውን እምነት ፡ የምንመሰክረውን ቃል የሚያስረዳ ነው ።

ይኸም ፡ መጽሐፍ ቅዱስ "… እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ።

ዓለም በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈጠረ በሃይማኖት እናምናለን።

እግዚአብሔር እርሱ አምላክ እንደሆነ ዕወቁ እርሱም ፈጠረን እኛም አይደለንም ።" የሚለውን ያጠቃለለ ቃል ነው ። ዘፍ· ፩ ፡ ፩ ። ዕብ· ፲፩· ፪ ። መዝ· ፳፬ ፡፪ ። አሁን ምን ጊዜም ሃይማኖት ስንል ፈጣሪ አለ ብሎ ማመን ማለታችንን ተገንዝበናል ።

ለሃይማኖትም ከርሱ ጋር የተያያዙ ዘርፎች አሉት ፡ ዘርፎቹን ጨምረን ስንጠቅስ ሥርዓተ ሃይማኖት እንላለን ።

## ከአበው ሲያያዝ የመጣ

ሥርዓተ ሃይማኖት በአማርኛ የሃይማኖት ሥርዓት ስንል

፩· የሃይማኖት ውሳኔ እና ድንጋጌውን ፡ ሃይማኖት ከዚህ አይተናል አይቀነስ ፡ ከዚህ አይለፍ አይተረፍ ፡ መባሉን መናገራችን ነው ፡

ኢትወስኩ ላዕለ ዝ ቃል … ወኢታንትጉ እምኔሁ አማርኛ በዚህ ቃል ላይ አትጨምሩ ፡

ከዚህም አታጉድሉ እንደተባለው ነው ። ዘዳ·፬·፪ ። ፲፪፡፴፪ ።

፪ኛ የሃይማኖት ሥርዓት ስንል የሃይማኖትን ስልትና አቀማመጡን የአቀማመጥ ቅደም ተከተሉን ፡ መናገራችን ነው ።

ይኸውም ስልት ማለት የዘርፉ ዓይነት ሲሆን አቀማመጥ ፡ ደግሞ የትምህርቱ አቀራረብ ተራው ነው ።

### የትምህርቱ አቀራረብ

ሥርዓተ ሃይማኖትን ቀጥሎ ባለው ተራ እንማራለን ።

ሥርዓተ ሃይማኖት የተሰኙ አርእስተ ነገራት

፩· ሥነ ፍጥረት የሚባለው ነው

፪· ነገረ ሃይማኖት (አዕማደ ምሥጢር የሚባለው

፫·ሕገ እግዚአብሔር ወይም ሕገ አምላካዊ

፬· ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን

፭· ነገረ ዓበቅቱ ወይም ሐሳበ ዘመን

፮· የሃይማኖት ታሪክ ወይም የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በመባል ይዘረዘራሉ ።

እነዚህን ስድስት አርእስተ ነገራት ከዚህ ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታቸዋለን ።

### ፩· ሥነ ፍጥረት

ሥነ ፍጥረት የተባለው ትምህርት ፡ በአራት ዘፍጥረት በምዕራፍ አንድ ካንድ ቁጥር እስከ ሃያ ስምንት ቁጥር ተመዝግቦ የሚገኘው የስድስቱ ዕለታት ፍጥረት ነገር እና በም ፪ ካንድ ቁጥር እስከ ሦስት ቁጥር የተነገረው የዕረፍተ ሰንበት ነገር ነው ።

ነገረ ፍጥረት እንዴት ነው ?

ነገረ ፍጥረትን የምንማረው (ሀ) በመጽሐፍ ቅዱስ (ለ) በቤተ ክርስቲያን መምህራን ዝግጅት ነው ። በመጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ እንማራለን ።

የመጀመሪያው ዕለት…

አሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፩ ከቁጥር ፩ እስከ ፭

እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ። ምድር ግን ጥንት ባዶዋን ነበረች ፡ አትታይም ነበረ ፡ ዝግጁም አልነበረችም ፡ ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ ፡ የእግዚአብሔር መንፈስም (ነፋስ) በውኃ ላይ ይሰፍ ነበር ። እግዚአብሔርም ብርሃን ይሁን አለና ብርሃን ሆነ ። እግዚአብሔርም ብርሃኑን መልካም እንደሆነ አየ እግዚአብሔር ጨለማንና ብርሃንን ለየ ፡ ብርሃኑንም እግዚአብሔር ቀን ብሎ ጠራው ጨለማውንም ሌሊት ብሎ ጠራው ፡ ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ አንድ ዕለትም ሆነ ይላል ፡ ይህም ዕለተ እሑድ የምንለው ነው ።

ከአሪት ዘፍጥረት አሁን ከጠቀስነው ክፍል በስም በስማቸው የተጠቀሱትን ፍጥረታት ለይተን እናስተምጥና እናያቸዋለን ፡ እነርሱም ሰማይና ምድር ውኃና ነፋስ ጨለማና ብርሃን ናቸው ። ምድር ባለው መሬት መሆኑን እንገነዘባለን ።

በዚህ በተነበበው ክፍል ያልተጠቀሱ ሌሎች ፍጥረታትንም በመጽሐፍ ቅዱስ እናገኛለን ። እነርሱም እሳትና መላእክት ናቸው ፡ እነዚህ ፍጥረታት መኖራቸውን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል ይናገራል ።

ስለ እሳት

ዘፍ· ፲፱፡፳፬ – እግዚአብሔር … እሳትንና ዲንን አዘነመ ። ዘዳ፡ ፴፪፡፳፪ እሳት ከቁጣው ትነዳለችና ።

መዝ·፻፵፰፡፯–፰ እግዚአብሔርን ከምድር አመስግኑ … እሳትና በረድ ።

ስለመላእክት

ኢዮብ ፴፰–፯ አመ ተፈጥሩ ከዋክብትየ ሰብሑኒ ኩሎም መላእክትየ (ባማርኛ) ከዋክብቱ በተፈጠሩ ጊዜ መላእክቱ ሁሉ አመሰገኑኝ ። መዝ·፻፫፡፬ መላእክቱን መንፈስ የሚያደርግ ፡ አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል ። መዝ·፻፵፰ ፡ ፪ና ፭ መላእክቱ ኹሉ አመስግኑት … እርሱ ሁኑ ብሎ ሁነዋልና ፡ እርሱ አዘዘ ተፈጥረዋልና ። በማለት በተፈጥሮ ያወሳቸዋል እሳትንና መላእክትን ።

በቤተ ክርስቲያን ትምህርት አቀራረብ እንዲህ እንመራለን ።

ከዚህ በላይ በገለጽነው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት ፡ የቤተ ክርስቲያን መምህራን (ሊቃውንት) የእሑድን ፍጥረታት አገልተው ፡ እንዲህ ያስተምራሉ ፡ እግዚአብሔር ፈጣሪ ፡ በመጀመሪያው ዕለት እሑድ ስምንት ፍጥረታትን ፈጠረ ፍጥረታትም

ሀ ጨለማ አንድ

ለ አራት ባሕርያት አራት ሲደመሩ አምስት

ሐ ሰባት የብርሃን ሰማያት አንድ ሲደመሩ ስድስት

መ መላእክት የብርሃን ሰማያት አንድ ሲደመሩ ሰባት

ሠ ብርሃን የብርሃን ሰማያት ሲደመሩ ስምንት

በቁጥር ብቻ የተጠቀሱት በስም ይገለጻሉ

አራቱ ባሕርያት ፩ኛ ባሕርየ እሳት

፪ኛ ባሕርየ ነፋስ





www.ethiopianorthodox.org

፫ኛ/ ባሕርየ ማይ
፬ኛ/ ባሕርየ መሬት ናቸው ።
ሰባቱ የብርሃን ሰማያት
፩ኛ/ ጽርሐ አርያም
፪ኛ/ መንበረ - መንግሥት
፫ኛ/ ሰማይ ውዱድ
፬ኛ/ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት
፭ኛ/ ኢዮር
፮ኛ/ ራማ
፯ኛ/ ኤረር ይባላሉ ።
ብዙ ሰማያት እንዳሉ መጽሐፍ ቅዱስም ይናገራል ።
ሀ/ መዝ ፻፳ ፥ ፳ እግዚአብሔር ግን ሰማያትን ሠራ ። መዝ ፻፴፭ ፥ ፭ ። ኢሳ ፵፩ ፥ ፲፫ ፲፯
ለ ዘዳ ፲ ፥ ፲፬ እንሆ ሰማይ የሰማያትም ሰማይ የአምላክህ የእግዚአብሔር ነው ።
ሐ መዝ ፻፵፫ ፥ ፭ አቤቱ ሰማዮችህን ዝቅ አድርገህ ውረድ ።
መ የሐ ፩ ፥ ፶፪ ትሬእዩ እንዘይትረኀዋ ሰማያት በአማርኛ ሰማዮች ሲከፈቱ ታያላችሁ ። ጳውሎስ ሐዋርያውም " እስከ ሦስተኛ ሰማይ ተወስጄ ነበር" ይላል ፪ ቆሮ ፲፪ ፥ ፪ ።
አስተውል አሁን ልዩ ስምና ቁጥር ባይጠራም መጽሐፍ ቅዱስ ሰማያት የሚላቸው ከላይ በአየስማቸው የተጠቀሱት ሰባቱ ሰማያትን እንደሆነ በዚህ እንገነዘባለን ።
የመላእክት ሁኔታቸው ከእሑድ ፍጥረታት ተለይተው መላእክት ሕያዋን ፣ ለባውያን ፣ ነባብያን ፣ ናቸው ፣ በዚህ ሁኔታቸው ፈጣሪያቸውን ይመስሉታል ።
በአካል መንፈሳውያን ማለትም ረቂቃን ናቸው ። "መላእክትሁ ሉ መልዕክት የሚላኩ መናፍስት አይደሉምን" ዕብ ፩ ፥ ፲፬ ። መዝ ፻፫ ፥ ፬
የዚህ ዝግጅታችን ማስረጃ ሀ በመጽሐፈ ሥነ ፍጥረት በአክሲማሮስ
ለ በመጽሐፈ ቀሌምንጦስ
ሐ/ በኩፋሌ በምዕራፍ ፪ ይገኛል ።

በተጨማሪም የካቲት ፲፭ ቀን ፲፱፻፹ ዓ/ም የታተመ ሥርወ ሃይማኖት የተባለውን መጽሐፍ ተመልክቶ ማገናዘብ ለዝግጅታችን ማስረጃነት አሁን የተጠቆሙት መጻሕፍት ከቤተ ክርስቲያናችን መጻሕፍት በከፊል መሆናቸውን እንዘነጋም ።
ለ/ የሁለተኛውን ዕለት ፍጥረት
በመጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ እንማራለን
ዘፍ ፩ ፥ ፯ ፰ እግዚአብሔር አለ፥ በውኆች መካከል ጠፈር ይሁን በውኃና በውኃ መካከልም ይከፈል ፣ እንዲሁም ሆነ ። እግዚአብሔርም ጠፈርን አደረገና ከጠፈር በታችና ከጠፈር በላይ ያሉትን ውኆች ከፈለ ። ጠፈርንም እግዚአብሔር ሰማይ ብሎ ጠራው መልካም እንደሆነም አየ ። ሌሊትም ሆነ ፣ ጧትም ሆነ ሁለተኛም ዕለት ኾነ ። ይላል ሁለተኛውም ዕለት ሰኞ የምንለው ነው ።
በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ዝግጅት እንዲህ እንማራለን
ከእሑድ እስከ ሰኞ ማለትም እሑድ ሌሊት ቀኑን ከምድር እስከ ብሩህ ሰማይ ውኃ ሞልቶ ነበር ፣ በሁለተኛው ዕለት ሰኞ ፈጣሪ እግዚአብሔር "በውኆች መካከል ጠፈር ይሁን" ብሎ በመናገር ውኃውን እንደ መስተዋት አጽንቶ በውኃው መካከል ጠፈርን ፈጠረ ፣ ጠፈር ማለት የውኃ ስር (ከውኃ የተሰራ) ማለት ነው ። ጠፈርም በተፈጠረ ጊዜ የሞላውን ውኃ ወደ ላይና ወደታች ከፍሎታል ። ኩፋሌ ፪ ፥ ፱ ። እግዚአብሔርም ጠፈርን ሰማይ ብሎ ጠራው ይህም ከምድር በላይ የሚታየው ሰማይ ነው ። ለጠፈር ሁለተኛ ስም አለው ምጽንዓት ይባላል ። ኩፋሌ ፪ ፥ ፱ ።
አሁን ከጠፈር በታች ውኃ እንደሞላ ነው ያለ ፣ ምድር ገና አልታየችም ። የሰኞ ፍጥረት አንድ (ጠፈር ብቻ) ነው ከእሑድ ፍጥረታት ሲደመር የሰኞና የእሑድ ፍጥረታት ዘጠኝ ይሆናሉ።
ይኽን ለፈጠረ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይግባው ።

ይቀጥላል ።

# ስለቅዳሜና እሁድ አከባበር

ከብፁዕ አቡነ ኤልያስ ሊቀ ጳጳስ

በዘመነ ብሉይ ቅዳሜ በየሳምንቱ በቤተ አይሁድ ዘንድ በጥንቃቄ ትከበር ነበር ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈሳዊ ሕግና ሥርዓት ምሳሌ የሚሆን ሕግና ሥርዓት ሲካሄድባት የኖረችውን ዕለት በሐዲስ ተፈጥሮ የመዳን ሥራው ወቅት የሥራ ቀን በማድረግ በይበልጥም በከርሠ መቃብር ውስጥ ቀድሞ ሲል አይሁድ በየጊዜው ምክንያት እንዳደረጉት ስለሰው ልጅ ድኅነት ነፍስ ምሳሌ ለሆነው ድኅነት ሥጋ በተአምራት መግለጽ ተዳይ የማዳን ሥራውን በመሥራት እንደሻራት በኋላም የሐዲስ ተፈጥሮ ሥራውን በዚች ዕለት ፈጽሞ በዕለተ እሁድ ከሌሊቱ ጀምሮ መቃብር ከፈቱልኝ መግነዝ ፍቱልኝ ሳይል ሞት ያመጣውን ሁሉ ዕዳ በደል አጥፍቶ ተነሳ ለትዱሳት አንስት ተገልጾ በዚህ ምክንያት መላእክት ከመቃብሩ አጠገብ በነጭ ልብስ በለበሱ ሰዎች አምሳል ታዩ ዕለቲቱ የደስታ የነፃነት ቀን ሆነች በዚህ ጊዜ ጌታ በሐዲስ ተፈጥሮ ከማዳን ሥራው ያረፈበት ቅድስቲቱ የጌታ ቀን ተባለች ሐዋርያት ከጌታችን ትንሣኤ በኋላ ትንሣኤውን ለማሰብና የክርስቶስ ተከታዮች መሆናቸውንም ለመግለጽ የመጀመሪያውን ቀን እሁድን አከበሩ የሐ ፳ ፲፱ ጌታም በዝግ ቤት ገብቶ አነጋገራቸው ቀደም ሲልም በዘመነ ብሉይ በዓመት አንድ ጊዜ (በዓለ ሠዊት) በመባል ትከበር ስለነበረች በዚሁ ልማድ በየሀገሩ የአይሁድ እምነት ተከታዮች ሁሉ ለማክበር እንደተሰበሰቡ መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት ወረደላቸው የቤተ ክርስቲያን መመሥረቻ ቀን ሆነች በዓለም ሕዝብ የታወቀች መሆኗ ታወቀ የሐዋ ፪ ፩ ፲፫ ። ዘፍ ፳፫ ፲፮ ። ፲ኛ ቆሮ ፲፮ ፪ ። ራዕይ ፩ ፲ የጌታ ቀን የተባለች እሁድ መሆኗን እንረዳለን ። እንግዲህ በዚህ መሠረት ከአንድ መቶ እስከ ሁለት መቶ ዘመን የነበሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የጻፉት የሚከተሉት ናቸው።
በአንድ መቶ ዓመትም የጻፈ
በርናባስ
ከአንድ መቶ እስከ መቶ ሰባ ዓ ም የጻፈ
አግናጥዮስ
በአንድ መቶ አርባ ዓ ም የጻፈ
ጀስቲን ማርቲን
በሁለት መቶ ዓም ገደማ የጻፈ ተርታሊዮን የተባሉ አበው እሁድ ሰንበትን ያከብሩ እንደነበር በየድርሳናቸው በሰፊው መስክረዋል።
ስለዚህ እሁድን ማክበር የክርስቲያን ምልክት ነው በምሳሌው ቅዳሜ ለእስራኤል ሕዝብ ምልክት እንደነበር ዘፀ ፴፩ ፲፭ ሕዝ ፳ ፲፯ ፳ እንዲሁም በሥጋዊው ወይም በእማናዊው እሁድ የቤተ ክርስቲያን ምልክት ነው ።
እግዚአብሔር እስራኤልን (የሚአከብራቸውና)የሚቀድሳቸው ለመሆኑ ቀዳሚት ምልክት እንደነበረች እንዲሁም ለመንፈሳዊ ወይም ለእስራኤል ዘነፍስ ለቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ሰውን ታርቆ አምላኩ መሆኑን ክርስቲያኑም ልጁ ወይም ሕዝቡ መሆኑን ያመለክታል ኢር ፴፩ ፴፩ ።
መጀመሪያው ቀን የእግዚአብሔር መጀመሪያ መፍጠር ምልክት እንደሆነ እንዲሁም የሁለተኛ ወይም በሐዲስ ተፈጥሮ በመ



ብፁዕ አቡነ ኤልያስ

ፈጠሩ ምልክት ነው ፪ቆሮ ፭ ፲፯። ኤፌ ፪ ፲ እንዲሁም ከሆነ እሁድ የክርስቲያን ምልክት ናት ይኸውም በመሆኑ ከቤተ አይሁድም ሆኑ ከአሕዛብ ወገን በክርስቶስ ያመኑት ሁሉ የቅዳሜን መሰብሰብ ወደእሁድ በመለወጥ እሁድን የእግዚአብሔር ቀን በማለት ያከብራሉ ።
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም በዚች ዕለት በልዩ ልዩ የመዝሙርና የመለች ምዕመናኖችም ከዋዜማው ጀምረው ቃለ እግዚአብሔር በመስማት የተጣላ በማስታረቅ ሥጋውን ደሙን በመቀበል ከተግባረ ሥጋ በማረፍ ለተግባረ ነፍስ ጽሙዳን በመሆን ያከብራሉ ።

# ቅዳሜንአክባሪዎች

የእለተ እሁድ አከባበር እንዲህ እንዳየነው በቅዱሳት መጻሕፍት የተረዳና የታወቀ ሲሆን ያለ በቂ ምክንያትና አስረጅ እንደገና ወደኋላ በመመለስ እሁድን ትተው ቅዳሜን ማክበር የጀመሩ የሰባተኛውን ቀን አክባሪ ተብለው የሚጠሩ በልዩ ልዩ ሀገሮች የተስፋፉ ድርጅቶች ይገኛሉ ስለ አጀማመራቸውና ስለአላማቸው ለአንባቢዎቻችን በመጠኑ እንገልጸለን ።
በ፲፱፻፲፫ዓ ም እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ማለት በ፲፰ኛው መቶ ዓ ም አንድ ውልየም ምለር የተባለ የአሜሪካን ሀገር ገበሬ መጽሐፍ ቅዱስን እያነበበ ሐሳቡን በትንቢተ ዳንኤል በምዕራፍ ፰ ቁ፲፫ ና ፲፬ ላይ መሥርቶ የክርስቶስ ዳግምምጽአት በ፲፰፻፵ ዓ ም በጥቅምት ወር ይሆናል ብሎ በብዙ ያስተምር ጀመር ።
ተጥሎ በ፲፰፻፸፪ዓ/ም ፍሬድሪክ ዊሰር የተባለ የአንድ ጸሎት ቤት መሪ የውል የምስርን ትምህርት ተቀበለና ከአሥርቱ ቃላት አንዱን የቅዳሜ ማክበርን መጠበቅ እንደሚገባ ማስተማር ጀመረ ራያቸል ፕሬስተን የተባለች ሴት ደግሞ ፍሬዶሪክ ቼለር ወደነበረበት መጥታ የቅዳሜን ነገር በብዙ ስለአስተማረች ፵ የሚያህሉ ሰዎች ቅዳሜን ማክበር ጀመሩ የአድቬንትስቶች ማኅበር አጀማመር ይህ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

# የቤተ ክርስቲያን አመሠራረት

ካለፈው የቀጠለ

ከብፁዕ አቡነ በርናባስ ሊቀ ጳጳስ

ስለቤተ ክርስቲያን አመሠራረት በአጭሩ እንመለከታለን ሁል ጊዜ ስለክርስቶስና ሃይማኖት ስለ ቤተ ክርስቲያን በምንናገር በት ጊዜ ሁሉ ትዝ የሚለውን የምናስታውሰው የቀደመው ሰው የአዳምን ሁኔታ ነው መጽሐፍ ቅዱስ እንደነገረን እግዚአብሔር የሁላችን አባት አዳምን ከፈጠረው በኋላ ባረከው ሁሉንም እንዲገዛ አደረገው ሥልጣኑንም ሰጠው ዘፍ፡ ፩፡፳፯-፴

በረከቱንና ሥልጣኑን ሲሳዩን ከሰጠው በኋላም ፈጣሪውን የሚ አስታውስበት ትእዛዝ አዘዘው እሱ ግን በተሳሳተ ምክር ተመርቶ ከፈጣሪው ትእዛዝ ወጣ በዚህም ጊዜ የሞት ፍርድ ተፈረደበት ዘፍ ፫፡፩-፲፱ ይህም የሞት ቅጣት ለእሱ አቅም ቀላል አልነበረም በሱም ብቻ አልቀረም የልጅ ልጆች ሁሉ ይህን የሞት ጽዋዕ ተካፈሉ ሮሜ ፭፡፲፪ ፡

አዳምና ልጆቹ ሕግን በመተላለፍ ከእግዚአብሔር ስለራቁ እውነተኛ አምላካቸውን እየዘነጉ የሰማይና የምድርን ሠራዊት ማምለክ ጀመሩ ማለት በጨረቃና በፀሐይ በከዋክብትም በእሳት በውኃ በእንስሳትና በአራዊት በዛፍና በተራራ ዘፍ ፬፡፲፱

ነገር ግን እግዚአብሔር የሰውን ዘር ጨርሶ ለመደምሰስ ስላልፈለገ በአንድ አምላክ በማመን ይህን የሰው ልጅ መራራና አስቀቂ ታሪክ ከመጀመሪያ ጀምረው ሲከታተሉ የነበሩ ጥቂት ጉሳዎች ነበሩ ለእነሱም ብዙ ጊዜ ሕጉንና ትእዛዙን ይሰጣቸው ነበር ብዙ ጊዜ ተአምራት ያደርግላቸው ነበር ዘፍ፡ ፲፪-፳፩ ነገር ግን በአካባቢው በነበረው ተጽዕኖ ምክንያት እነዚህ ሰዎች አልፎ አልፎ በየጊዜው ወደ አምልኮ ባዕድ ይወድቁ ነበር ይሁን እንጂ ከእውነተኛው እምነት ያላፈነገጡ በአምልኮተ ባዕድ ያልተለወጡ እስራኤላውያን ነበሩ ነገሥ፡ቀ፡፲፱-፲፰

በዚህም ላይ ከኃጢአት ለመንጻትና የእግዚአብሔርን ምሕረትና ይቅርታ ለመጠየቅ ያላደረጉት አልነበረም ከጥረታቸውም የተነሣ የተለያዩ የመሥዋዕት ዓይነቶችን ያቀርቡ ነበር ያቀርቧቸው ከነበሩትም ጥቂቶችን እጠቅሳለሁ ብዙ ወይፈኖችንና ጊደሮችን እንዲሁ ሌሎችን የመሳሰሉትን ሁሉ ያቀርቡና ይሰው ነበር ፡ ዕብ፡ ፱፡፳፭ ከዚያም ሌላ እግዚአብሔርን ደስ ይበለው በማለት በወርቅ የተለበጠ በሐር የተጨመጨመ ቤተ መቅደስም ሰርተው ነበር ፡

እግዚአብሔር በነቢያት ‹እያደረ የሚመልሰው መልስ ግን ይህን ሁሉ ደስ ብሎት የተቀበለው አይመስልም ከዚህ ሁሉ የሰው ልጅ የታሪክ ጉዞ በኋላ እግዚአብሔር በራሱ ፈቃድ የሰውን ልጅ ለማዳን የቀጠረው ቀን ሲደርስ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው ልጁን ሰው ይሆን ዘንድ ወደዓለም ልኮ በልጁ በክርስቶስ ሞት ቤተ ክርስቲያን የተወለደችው ወይም የተመሠረተችው በፍልስጥኤም ምድር ነው ።

ይህም የሆነበት ምክንያት ከላይ እንደተናገርነው የሰው ልጅ ትክክለኛ ታሪክና የእግዚአብሔርንም የምሕረት ተን በተስፋ ሲጠባበቁ የነበሩ ብዙ ደጋግና ቅዱሳን ሰዎች ስለነበሩበት የእግዚአብሔር የማዳን ሥራው ድንገተኛ ሳይሆን ለብዙ ዘመናት በተስፋ ሲጠበቅ የቆየ መሆኑን ለመግለጥ ነው ።

የሐ፡ ፰፡፶፯ የሰው ልጅ ከሚመጣበት ችግር ሁሉ ለመዳን ወይም የፈለገውን ነገር ለማግኘት ያላደረገው ጥረት አልነበረም ።



ብፁዕ አቡነ በርናባስ

ከአደረጋቸው ጥረቶች የሚከተሉትን እገልጻለሁ ።

፩ኛ አምልኮ ጣዖት ፡

፪ኛ ለጣዖቱ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ መሥዋዕቶችን ማቅረብ፡ ናቸው እነዚህ ጣዖታት ግን ዓይን እያላቸው የማያዩ እጅ እያላቸው የማይዳስሱ እግር እያላቸው የማይራመዱ አፍ እያላቸው የማይናገሩ ጆሮ እያላቸው የማይመልሱ የማይሰሙ ግዑዛን ፍጥረቶች ናቸውና አንዳችም የሚአረጋጋ ነገር ሊአደርጉላቸው አልቻሉም መዝ ፻፲፫ ከዚህ የተነሣ ሕዝቡ አምላኩች የዋሃንና ገጽ የለሾች ናቸው እያሉ በጣዖታቱ ያፌዙና ይዘብቱ ነበር።

የሰው ልጅ ሥልጣኑም በክፋትና በደግነት መካከል ያለውን ልዩነት ለመመልከት አልቻለም በዚህ አኳኋን ለሰው ልጅ የወደፊት ዕድል ምንም ዓይነት የተስፋ ጭላንጭል አልነበረም ሰው በተፈጥሮው ከየት መጣሁ ወዴትስ ነው የምሄደው ብሎ ራሱን በራሱ የመጠየቅና የመመርመር ስጦታ ያው ባለአእምሮ ፍጡር ስለሆነ ሁልጊዜ እነዚህ ጥያቄዎች በፊቱ ይደቀኑበታል ነገር ግን ለዚህ ጥያቄው ከውስጥ ከራሱም ሆነ ከውጭ ከሌላው አጥጋቢ መልስ ለማግኘት ስላልቻለ ከላይ እንደተገለጠው ምንም እንኳን በደስታ ቢኖርም የደስታውን ጣዕሙንና ምስጢሩን ሊአወቀው አልቻለም በዚህ ሁኔታ ሰዎች በኃዘንና በተቢጸ ተስፋ ስለተሞሉ እነሱም ሆኑ ማኅበራዊ ኑሯቸው ጠባቂ እንደሌለው መንጋ ወይም ቀዛፊ እንደሌለው መርከብ አቅጣጫው የማይታወቅ ሆነ ይህ ሁሉ የሁከትና የሽብር ጥላ ባንዣበበበት ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሠረት የአሕዛብ ብርሃን የእስራኤል ዘነፍስ ክብር መድኅን በሮም ቅኝ ግዛት ሥር በነበረች በፍልስጥኤም ልዩ ስሚ ቤተ ልሔም በምትባል በይሁዳ ዕፃ ተወለደ ማቴ፡ ፪፡፩ በተወለደ ጊዜ የመዳን ትንቢት ሰባዔ ያልተቆጠረባቸው አሕዛብ ሰብአ ሰገል መድኅን መወለዱን አውቀው ከምድረ አሕዛብ እጅ መንሻውን አመጡለት የመወለዱም ዓላማ ስለጽድቅ ለማስተማርና ለመመስከር በሞቱ የሰውን ዘር ከኃጢአት ለማዳን ነው ።

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

መሬት ለሰው ልጅ የተሰጠችው እንዲሁ እየተመለከታት እን ዲኖር ሳይሆን መሬትዋ በኃርፍ እንዳይሸረሸርና በነፋስም በየ በየ እንዳይጠፋ ሊጠብቃትና ሊን ከባከባት ነው የተሰጠችው

መሬትም በበኩልዋ በእንክብካቤ ስትያዝ ለሰው ልጅ የዕለት ምግቡን የዓመት ልብሱን ለመጠለያና ለማገዶ የሚሆኑት እንጨቶችን እጥፍ ድርብ አድርጋ ዋጋውን ለመስጠት ነው ።

ሰው ባለው አቅም እስከ ተቻለው ድረስ ያርሳል፡ ይቆፍራል ባረሰውና በቆፈረውም ላይ ልዩ ልዩ አዝርትን እየዘራ ያመርታል። የተለያዩ ዘሮችንም እየተከለ ይጠቀማል ።

በዚህ መሠረት መሬትን እያረስክ ተጠቀም በላብህም ወዝ እንጀራህን ብላ ባለው አምላካዊ ቃል መመሪያ መሬትን እያረሱና እያለሙ የሚጠቀሙ እጅግ ብዙዎች ናቸው ።

ከብዙዎቹም አንዱ በሲዳሞ ሀገረ ስብከት ከአዋሳ ዋና ከተማ በስተምዕራብ ስለሚገኘው የቤተ ክርስቲያን ልማት እንገልጻለን ።

በአዋሳ ያሉት ልማቶች እንደ ሚከተሉት ናቸው ።

የአትክልት ዓይነቶች
ብርቱካንና ሎሚ
ሙዝና ፓፓያ
ሽንኮር አገዳ
ወይንና ሮማን

ቡና ከዝሚርና ወሸሚላ
ተምርና አቡካዶ ሲሆኑ

ጓሮ አትክልት ደግሞ
ቲማቲምና ቃርያ
ቀይ ሽንኩርትና ቆስጣ
ካሮትና ቀይ ሥር
ድንችና ጥቅል ጎመን
የመሳሰሉት ናቸው

ከእህልም ዘሮች በቆሎና ቦሎቄ በብዛት ይመረታል ። በተለይ በፓፓያ በኩል ከተማውን ይዞት የሚገኝና በየቡና ቤቱ የሚጠጣው የፓፓያ ጭማቂ ከዚህ በቤተ ክህነት ከሚገኘው የፍራፍሬ ምርት ነው ።

የአትክልቱ ቦታ አራት ቀዋሚ ሠራተኞች ሲኖሩት ዙርያውም እሾሃማ በሆነውና ከሾናም በመባል በታወቀው አጥር የተከበበ ነው ።

የልማቱና የካህናቱ ማሠልጠኛ ሥራ አስኪያጅ መምህር ኃይለ ሥላሴ ግዛው እንደ ገለጹልን የአትክልቱ ቦታ ምንም እንኳ አራት በቀዋሚ ሠራተኛ የተቀጠሩ ቢኖሩም ካህናቱም በሚሠለጥኑበት ወቅት አንዳንድ ሥራ እንደሚያግዟቸው አስረድተውናል ።

በመሠረቱ መምህር ኃይለ ሥላሴ ስለ አትክልቱም ሆነ ስለእርሻው ሲያብራሩ ልማቱ የሚካሄደው በሁለት ዓይነት ነው ።

ይኸውም ግማሹ በእርሻና በቱፋር የእህል ምርት ሲመረት ግማሹ ደግሞ በአትክልት ተከላ ተውጦ ዘንድሮ እንኳን አሉ መምህር ኃይለ ሥላሴ ከአንድ ሺህ ያለነሰ ብርቱካን ተክለን እንሆ ጸድቆ በልምላሜ ይገኛል ብለዋል።

ይኸ ብቻ አይደለም ። በተተከለውም ብርቱካን ያሉን ተማሮች ዛፎችንና አትክልቶቹን በማዳቀል የሰለጠኑ ስላሉን እንሆ የተከልነው ብርቱካን በሙሉ ተዳቅሎ





www.ethiopianorthodox.org

ይገኛል ።

የሚያርሱና የሚያርሙ ደግሞ ፯ ሠራተኞች አሉን ። ሠራቶኞቹም ከሌላ የመጡ ሳይሆኑ በሙሉ ካህናት ናቸው ።

እነዚህም ካህናት እሁድ ይቀድሳሉ ፡ ወንጌልንም ይሰብካሉ ። በሌላ ቀን ግን በልማት ሥራ ተሰማርተው መሬትን ያለማሉ ።

ስለዚህም ካህናቱ በውጭ ያርሳሉ ፡ ይቆፍራሉ በቤተ ክርስቲያንም ኪዳንን በማድረስ በመቀደስና በማጠን ቤተ ክርስቲያንን ያገለግላሉ ።

በአዋሳ ያለው ፓፓያና የሸንኮር አገዳ ፍጹም ሜካ ስለሚመስል በጣም የሚያስፈራ ነው ። በአዋሳ የሚካሄደው የቤተ ክርስቲያን ልማት ዓይንን የሚማርክ አእምሮን የሚያድስ ሲሆን እስካሁን ድረስ አስፈላጊው ምርት ቢመረትበትም አንድ ችግር እንዳለበት የልማቱ ሥራ አስኪያጅ መምህር ኃይለ ሥላሴ ግዛው ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል ። ከዚህ የበለጠ ምርትን ማምረት ይቻል ነበር ። ነገር ግን ሥራ ያለ መሣሪያ ሊከናወን ስለማይቻል በዚህ ዓይነት ይታያል የውኃ መሳቢያ ሞተር ቢገኝ ሌላ ውጤት ማስገኘት በተቻለ ነበር ፡ ግን የውኃ ሞተር ባለመኖሩ ሥራው የተሟላ ነው ለማለት ያስቸግራል ብለዋል።

እዎ የልማት ቦታዎች አሉን ማለት በቂ አይሆንም ። ለእርሻ ትጉ ገበሬ ንቁዎች በሮችና ሞፈር ቀንበር ማረሻም እንደሚያስፈልጉት ሁሉ ።

ለአትክልተኛም ውኃ የሚያጠጣበት የውኃ ሞተር ያስፈልገዋል።

ስለዚህ ቢታሰብበት መልካም ነው ። ሌሎችም አድባራትና አብያተ ክርስቲያናት የዚህን የአዋሳ ልማት ተመልክታችሁ ብታለሙ መልካም ነው እያልን ሳንጠቁም አናልፍም ። ልማት የሕይወት ዋስትና ነውና ።

ክንፈ ርግብ ማርቆስ

# "ግብረ ኖሎት"

ከአለፈው የቀጠለ

ከሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገብረ አማኑኤል

ግብር ማለት ሥራ ፡ ኖሎት ማለት ደግሞ እረኞች ፡ ጠባቂዎች ማለት እንደሆነ በአለፈው ትንግሥ መጽሔታችን መግለጻችን ይታወሳል ። አጠቃላይ ይዘቱም የካህናቱን መሠረታዊ የክህነት ሥራና ከሊቀ ኖሎት ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበሉትን አደራ ከመግለጽ ጋር በኖላዊነታቸው (በጠባቂነታቸው) ለምዕመናን የሚሰጡትን ወይም የሚያበረክቱትን መንፈሳዊ አገልግሎትንና መግቦትን የሚገልጽ የክህነት አገልግሎት ነው ። በአጭር አገላለጥ የጠባቂዎች ጠባቂ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱን ቸር ጠባቂ፡ ምዕምናንን አባግዕ ብሎ የመሰየሙን ያህል ካህናቱም የሱን የማስተማርና የመግቦት ሥራ ስለሚሠሩ ኖሎት ተብለዋል ። "ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ ፡ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ መቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ አገልግሉ" በማለት ሐዋርያው ቅ ጴጥሮስ ያሳስባል ። (፩ኛ.ጴጥሮስ ፬:፲) እያንዳንዱ መጋቢ (ካህን) ከልዑል እግዚአብሔር የተቀበለውን ስጦታ የማወቅና የማሳደግ ፡ የማስፋፋትም ኃላፊነት አለበት የመጋቢነት ስጦታው በጥንቃቄ ከተያዘና ከተሠራበት ለአገልጋዩም ሆነ ለተገልጋዩ ከፍተኛ ዋጋን እንደሚያስገኝ እሙን ነው ። መረጃውም "አንተ የታመንክ በጎ አገልጋይ በጥቂት የታመንክ ስለሆንክ በብዙ እሾምሃለሁ ።" የሚለው ይሆናል ። (ማቴ.፳፭:፳፫)

የመጋቢነቱ ስጦታ የሚገኘው ከሊቀ ኖሎት ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ ቢታወቅም ተቀባዩም ለራሱ ክብር ማስገኛ አድርጎ ቢያውለው ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። ይህንንም ማድረግ የስጦታው ባለቤት የሆነውን እግዚአብሔርን አለማክበርም ነው ። ስለዚህ ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "የጌታውን ፈቃድ አውቆ ጌታው እንደ ወደደ የማይሠራ ፡ የማያዘጋጅም አገልጋይ ቅጣቱ ብዙ ነው" ሲል ያስተማረው ። (ሉቃ ፲፪:፵፯) ይህ ከሆነ እያንዳንዱ መጋቢ (ካህን) የመጋቢነቱን ሥራና ኃላፊነት ጠንቅቆ ማወቅና መረዳት ያስፈልገዋል ። በመሠረቱ የሰውን ልጅ እንደማንኛውም ሥነ ፍጥረት ለእንባቢያን አእምሮ በሚስማማና በሚረዳ መልኩ ማቅረብ ይቻላል ። ለምሳሌ አንድ ግንድ (ዛፍ) አበቃቀሉና አወጣጡ ቀናና ቀጥተኛ ሆኖ ቢበቅልም ከንቅርንጫፉና ከነቅጠሉ ለታቀደለት ዓላማ ሊውል ፈጽሞ አይችልም ።

መልክ ሰጪ በሆኑ መግረያዎች ተጠርቦና ፡ እንደአስፈላጊነቱ ተልጎ በሚያያዙ ነገሮች ተገጣጥሞ ፡ በቀለምና በዘይት ተቀብቶ ፡ መልኩና ውበቱ በአማረ አኳኋን ይዘጋጅና ከታቀደለት ዓላማ ላይ ይውላል ። አገልግሎቱንም ያበረክታል ። በምሳሌነት የተገለጸውን ግንድ (ዛፍ) ለተፈላጊው አገልግሎት እንዲውል የሚያደርጉት ጠበብትና ባለሙያዎች ናቸው ። አዕምሮአቸውን የጨመቁበት ፡ ጉልበታቸውን ያደከሙበት ሥራ ከቁም ነገር ላይ ውሎ ሲያውትና ሲጠቀሙበት የመንፈስ እርካታን ለአምሮአቸው ይፈጥርላቸዋል ። እንዲዚሁም የምዕምናን ጠባቂዎች ፡ አስተማሪዎችና መጋቢዎች የሆኑት ኖሎት (ካህናት) የሰውን ልጅ አእምሮ በትምህርተ ወንጌል አለስልሰውና አለዝበው ፡ በእምነትና በምግባር አጐልምሰው ለታቀደለት ግብ መንግሥተ ሰማያት የሚያበቁ የትምህርተ መለኮት ጠበብት ቀደም ሲል ነቢያት በጊዜያችንም ሐዋርያትና ተከታዮቻቸው ካህናት ናቸው ።

ይህንንም ፡ የምንልበት ምክንያት በፍጥረቱ ክቡር የሆነው ሰውምንም እንኳ በአእምሮ ጣባይዕ አዋቂ ቢሆንም ለእወቀቱ ድጋፍ ሰጪ የሆነ ምስሃ አከል ትምህርት ያስፈልገዋል ማለት ነው ። በክህነት አማካይነት በእግዚአብሔርና በሰው ዘንድ ተወዳጅነት ያላቸው ፡ የትምህርተ ወንጌል አርበኞች (ኖሎት) የምእመናን መሪዎችና መጋቢዎች ከምእመናን አእምሮ ኑፋቄን አስወግደው በእምነት አለምልመው በሥነ ምግባር አስውበው ለቅድስና ፍሬ ማብቃት ሐዋራያዊ ተልዕኮአቸው ነው ። ሊቀኖሎት ኢየሱስ ክርስቶስ "ቸር እረኛ እኔ ነኝ ፡ ቸር እረኛም ስለበጐቹ ቤዛ ሕይወቱን ይለውጣል።" (ዮሐ.፲.፲-፲፩) ሲል እንዳስተማረው መጋቢ ካህናት ፡ ስያሜ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን መስለው አርአያውን ተከትለው የመሥራት ግዴታ ያለባቸው ኖሎት (ካህናት) ናቸው ።

በተሰጠው ሀብት ላይ ጠቢብ የሆነ እያንዳንዱ መጋቢ ፡ ወደ ጌታው ደስታ እንደሚገባ ተምረናል ። (ማቴ.፳፭.፳፩) ስለዚህ የመጋቢነትን ኃላፊነት የተቀበለ ማንኛውም መጋቢ (ካህን) ከጌታው የተቀበለውን መክሊት (ሥልጣን) በትክክል ሊሠራበትና ሊጠቀምበት ይገባል ። ራሱን የእግዚአብሔር ንብረት ጠባቂ (መጋቢ) እንዲሆን አድርጐ መቁጠር ይኖርበታል ። እግዚአብሔር የንብረቱ ባለቤት እንደመሆኑ መጠን እንደሚፈልገው የእሱ የሆነውን ልንሰጠው ይፈልጋል ። የእሱ የሆነውን ከእንትርሩ ሊቀበል ሲመጣ አደራ የተሰጠውን መክሊት ያላበዛ አገልጋይ እድል ፈንታው "ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት" ባለበት በጨለማ ሥፍራ ለመኖር መዘጋጀት ነው ። (ማቴ.፳፭.፴)

# ዜና ሊቃውንት

## የስመ ጥሩው የመሪጌታ ጌታሁን ዓይኔ አጭር የሕይወት ታሪክ

መሪጌታ ጌታሁን ዓይኔ ከአባታቸው ከአቶ ዓይኔ አድገህና ከእናታቸው ከወ/ሮ ስመኝ ካሣ በጐጃም ክፍለ ሀገር በባሕር ዳር አውራጃ በይልማና ዴንሳ ወረዳ በታላቁ ቦታ በአዴት ደብረ መድኃኒት ገዳም በ፲፱፻፱፩ ዓ.ም. ተወለዱ ።

በዚህም መሠረት እድሜያቸው ለትምህርት እንደ ደረሰ የወላጆቻቸውን ቤት ሳይለቁ እዚያው ከአዴት በግምት ሦስት ኪ.ሜ ርቀት ላይ በምትገኘው በጥንታዊ ገዳም መካነ ቅዱሳን ደብረ ፍልስታ ማርያም በማስተማር ላይ ከነበሩት ከአባ ገብረ እግዚአብሔር ፊደል በመቁጠር ንባብና ዳዊት ከአወቁ በኋላ ትምህርታቸውን በመቀጠል ወደ ደብረ መድኃኒት ገዳም በመመለስ በጊዜው ከነበሩት ከመሪጌታ ይመር. . . ዐዋትወ ዜማን በሚገባ ተምረው ከጨረሱ በኋላ በዚሁ ሀገረ ስብከት እውቅ ከሆኑት ከመሪጌታ ገሠሠ ይስማላ ጊዮርጊስ ቅኔ ተምረዋል ። በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ ከብሉያት ፩ኛ. ነገሥትን ፪ኛ.ዳዊትን ፫ኛ. ከመጽሐፈ ሊቃውንት ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያምን አሂደዋል ።

ከዚያም አራት ዓይና ጎሹ ጉባኤ ዘርግተውበት ወደነበረው ታላቅ ቦታ ደብረ ገነት ሞጣ ጊዮርጊስ በመሔድ ከመምህር ገብረ ማርያም ቅኔውን ከመክለሳቸውም በላይ አገባቡን በሚገባ ተምረዋል ። ከዚህም እውቀታቸውን ለማስፋፋት በመንግሥቱና በዲማ የሚገኙትን ጉባኤ ቤቶች ቃኝተዋል ። እንደገናም የቅኔ ዩኒቨርስቲ በመባል ከሚነገርላትና ሰመጥር ወደሆነችው ደብረምዕራፍ ዋሸራ ማርያም በመሔድ በጊዜው ከነበሩት ስመጥሩ ወደሆኑት አለቃ ተክሌ ዘንድ ቅኔያቸውን ከነአገባቡ ተምረው በማወቃቸው ዳግም ተክሌ የሚባል የቅፅል ስም





www.ethiopianorthodox.org

ተሰቷቸዋል ። ከዚህ በኋላ አለቃ ተክሌ ሙያየንና እውቀቴን በሚገባ ስለያዝክ ከእንግዲህ መርቂህ ለሁና ሒድና ጉባዔ ዘርግተህ አስተምር ብለው መርቀው አሰናብተዋቸዋል ። በዚህ መሠረት መሪጌታ ጌታሁን ለመጀመሪያ ጊዜ የቅኔ ጉባያቸውን የጀመሩት በጐንደር ሀገረ ስብከት በደብረ ታቦር አውራጃ በእስቴ ወረዳ መካነ እየሱስ በተባለው ታላቅ ቦታ በ፲፱፻፳፭ ዓ/ም ሲሆን በዚህ ቦታም ለ፳ ዓመታት በተከታታይ አስተምረዋል ። እንደገናም ወደ ትውልድ ቦታቸው በመመለስ ከ፱፻ ተማሪ በላይ አስከትለው በአዴት ደብረ ቅዱሳን ሐና አዲስ ቦታ መስርተው የቅኔ ጉባያቸውን በሰፊው ተያይዘውት በማስተማር ላይ እንዳሉም ደግሞ ጌቴ ገሞራው እየተባሉ ይጠሩ ነበር ። በሕገ ቤተ ክርስቲያናችንም መሠረት ወ ሮ ጠጂን በሕግ አግብተው ሁለት ወንዶችና ሦስት ሴቶች ልጆችን ወልደዋል ።

መሪጌታ ጌታሁን ዓይኔ ከ፶ ዓመት በላይ እያስተማሩ ሲኖሩ ከራሳቸው ጥረትና ከተማሪዎቻቸው የጉልበት ሥራ እርዳታ በቀር ከመንግሥት ደመወዝ አያውቁም ነበር ። ሊቁ እያሳረሱ እራሳቸውን በራሳቸው ከመርዳታቸውም ሌላ ላጡና ለተቸገሩ ይረዱ ነበር ። መሪጌታ ጌታሁን መላ እድሜያቸውን ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ግስን ከመግሰስ ቅኔን ከመዝረፍ ተለይተው አያውቁም ነበር። መሪጌታ የቅኔ መምህር ብቻ ሳይሆኑ ስልጣነ ክህነትን ከመምህርነት ጋር አስተባብረው የያዙ ታላቅ አባት ነበሩ ። የቅስና ስልጣን የተቀበሉትም በሀገረ ስብከቱ በየጊዜው ከነበሩት ከአቡነ ማርቆስ መሆኑን በሕይወት እያሉ ይናገሩ ነበር ። ከጉባያቸው ስፋት የተነሣ ብዙ ደቀ መዛሙርትን ያፈሩ ሲሆኑ ከ፴ በላይ የቅኔ መምህራን ከማቸው ተመርቀዋል ። ከእነዚህም የቅኔ መምህራን ውስጥ ከአብራካቸው የተከፈሉት ልጃቸው መሪጌታ ይሔይስ ጌታሁን አንዱ ነበሩ ። ሌሎችም መሪጌታ ብዙ አየሁ መሪጌታ መሠረት፡ መሪጌታ ተአምር ወዘተ ይገኛሉ መሪጌታ ጌታሁን አይኔ ከሌሊቱ ፲ ሰዓት ጀምረው እስከ ጧት ፬ ሰዓት ድረስ ቅኔን በመዝረፍ ግሥ በመግሠሥና የመጻሕፈ ነገሥት ትርጓሜን የሚያሰሙ ሲሆኑ ከ፫ ሰዓት እስከ ፰ ሰዓት ደግሞ ቅኔ በማስነገር ከዋሉ በኋላ የዕለት ጸሎታቸውን አድርሰው እህልና ውሃ የሚቀምሱት ከቀኑ ፲ ሰዓት ላይ ነበር ። ሊቁ በቀን ከ፬ና ከ፫ ሰዓት ያልበለጠ የዕረፍት ጊዜ ነባራቸው ከላይ እንደተገለጸው ከ፶ ዓመት በላይ አስተምረዋል ምንም እንኳ ደግና ቅን ቢሆኑም ሞት ሥጋን ለለበሰ ፍጡር ሁሉ የማይቀር በመሆኑ በተወለዱ በ፹፫ ዓመታቸው መጋቢት ፳፩ ቀን ፲፱፻፸፫ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ። ዜና እረፍታቸውም እንደተሰማ የደብረ ቅዱሳን ቅድስት ሐና ሊቃውንትና ካህናት የመካነ ቅዱሳን ደብረ ፍልሰታ ማርያም ሊቃውንትና ካህናት እንደዚሁም የደብረ መድኃኔ አዴት መድኃኔ ዓለም ሊቃውንት ካህናት በአካባቢው የሚገኙ የገዳማት አበምኔቶች የደብር አለቆችና ሊቃውንት በሺህ የሚቆጠሩ ሕዝበ ክርስቲያን በተገኙበት በአዴት ደብረ ቅዱሳን ሐና ቤተ ክርስቲያን ያቀብራቸው ሥነ ሥርአት ተፈጽሟል ።

<u>ሊቁ መሪጌታ ጌታሁን ዓይኔ ከተቀኟቸው ቅኔዎች አንድ መወድስ ቀጠለን እናቀርባለን</u>

አምላክ አበዊነ ሞት እግዚአብሔር ፡ ለእመ ይመጽእ ግብተ ከመ ሠራቂ ይጠይቀነ ፡ ዘእንበለ ፍሬ ረከባ ለዕፀ በለስ ዕድሜነ ፡

ወነበረት እንዘ ትረድእ ማርታ ሥጋነ ፡

በመብልዕ ወበመስቴ ፡ ለእግዚአ ኩሉ ዓለም ኅቤሁ ዘአ ቅረበነ፡

<u>ለዓለም</u>

አመ ሀልቀሂ ወተፈጸመ ምግባረ ሠናይ ስንቅነ ፡

ለሐዊረ ርሁቅ ፍኖተ ጽድቅ ጸመውነ ወደከምነ ፡

ወተረፈ አበው ዕረፍተ ለአመ ሰአልነ ፡

መንግሥተ ሰማያት እመኩሉ ኢትቄሙ ትበለነ ፡

<u>ትርጓሜ</u>

የአባቶች አምላክ እግዚአብሔር ሞት በድንገት እንደሌባ ሲመጣ ዕፀ በለስ ዕድሜያችንን ያለ ፍሬ ያገኛታል ።

ማርታ ሥራችን ወደ እርሱ ያቀርበንንና የሁሉም ጌታ የሆነውን ይህን ዓለም በመብልና በመጠጥ ስታገለግለው ኖረች ።

<u>የለዓለሙ ትርጉም</u>

መልካም ምግባር ሥንቃችን ባለቀ ጊዜ የጽድቅ ጐዳና ወደሆነች ሀገር ለመሄድ ደከምን የአባቶች ፍርፋሪ ዕረፍትን በለመን ጊዜም የሁሉ እናት የሰማይ መንግሥት አትቁሙ አለችን ማለት ነው ።

ከተማሪዎቻቸው አንዱ
ኢሳያስ ደምለው ።



# የቅድስት ሐና ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ባጭሩ

የቅድስት ሐና ቤተ ክርስቲያን የምትገኘው በመንዝና ግሼ አውራጃ በመሐል ሜዳ ገፈገፍ ከሚባል ቦታ ላይ ነው ከመሐል ሜዳ ከተማ ፬ሰዓት ያስኬዳል ።

ቦታው ለጥ ያለ ሜዳ ሁኖ ብዙ ምንጮች ሚመነጩበት ለምለም ማር ዘወትር የማይለይበት የደስ ያለው መልካም ቦታ ነው በዚህም ቦታ ላይ ዓፄ ዘርያዕቆብ ለሥራ ጉዳይ ሲያልፉ ድንኳን አስተክለው አድረው ሳሉ ቅድስት ሐና ልጇን እመቤታችን ቅድስት ሐናን ታቦት አስገብተው ቅዳሴ ቤቷን አከብረው ሒዱ የሚል ታሪክ ተጽፏል ።

ከዚያን ዘመን ጀምሮ ይህች ታቦተ ሐና ልዩ ልዩ ተአምራት ትሠራ ጀመር በዓፄ ዘርአያዕቆብ ዜና መዋዕል መጽሐፍ ላይ ተጽፎ እንዳገኘነው ግራኝ መሐመድ በዓፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት በዓመጽ ተነሥቶ የኢትዮጵያን ታሪካዊ ቦታዎች ለማጥፋት በዚችው ገፈገፍ ሐና አጠገብ በብዙ ሠራዊት ሁኖ ሲያልፍ የተቀመጣባት በቅሎ ደንብራ ግራኝ መሐመድን ከመሬት ፈጥፍጣ ጣለችው በዚህ ተናዶ ቤተ ክርስቲያኒቱን አቃጥሏት ብሎ አዘዘ ወታደሮችም ለማቃጠል ቢሞክሩ አልቀጣጠልም ብላ አስቸገረች ።

ግራኝ መሐመድም ይህን ጉዳይ ተመልክቶ ግንቡንና ጣራውን አፍርሱት ብሎ ሠራዊቱ ሙከራ ሲያደርግ ኃይለኛ ነፋስ ተነሥቶ ግራኝ መሐመድን ከነሠራዊቱ እንደወባ በሽታ እያንቀጠቀጠ አባርታል ።

የግራኝ በቅሎም ገብታ ተንኮታኩታ ዕለቱን ሙታለች ቤተ ክርስቲያኒቱም ምንም ጉዳት ሳይደርስባት ተገኝታለች ይባላል ። በዚህ ምክንያት የሀገሬው ሕዝብም ቅድስት ሐና ሆይ መመኪያችንና መኩሪያችን ቤዛችንን እግዚአብሔር ስለሰጠን ደስታችን እጽፍ ድርብ ነው እያሉ ለቤተ ክርስቲያኗ ብዙ ልዩ ልዩ ስጦታ አድርገዋል ።

፬ኛ. በዓፄ ናኦድ ዘመነ መንግሥት ከቤተ ክርስቲያኒቱ ቅጽር ግቢ ከመቃብር ቤት እሳት ተነሥቶ አራት መቃብር ቤትና ደጀ ሰላሙ ሲቃጠል በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ምንም አደጋ ሳይደርስ በተአምር ድናለች በቤተ ክርስቲያኒቱ ብዙ ዓፀዶች አሉ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያኗ ክዳን ላይ ወድቀው ጉዳት እንዳያደርሱ በተአምራት ተጣመውና ተቆላመው ወደ መሬት አዘንብለው ይኖራሉ ።

በዚህም ግንድ አጥን የሚባል የቅጽል ስም ወጥቶላት እስካሁን ትጠራበታለች ይህም ማለት ቅድስት ሐና እንኳንስ ጠላቷን ግንድ ታጣምማለች ማለት ነው ታቦቷም ፈጥና ሰሚ ስለሆነች የቤተ ክርስቲያኒቱ አፈር ለአይጥና ለእሳት አደጋ መድኃኒት ነው እየተባለ የታጠነበትን አመድና የመሬቷን አፈር ለመውሰድ ከየአቅጣጫው የሚመጣው ሕዝብ እጅግ ብዙ ነው ከዚህም ተአምረኛ ቤተ ክርስቲያን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፲፰ ቀን ሱባኤ አድርገው ሰንብተው በሚመለሱበት ጊዜ የንዋየ ቅድሳትና የገንዘብ እርዳታ ከማድረጋቸውም በላይ በግል ገንዘባቸው ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ውስጥ አሁን በቅርቡ ተቆፍረው ፫ ዋሻዎች ተገኝተዋል በውስጣቸው የመልአኩ የቅዱስ ገብርኤል ጽላት የቅድስት ጽላት የቅዱስ ሩፋኤል ጽላት ተገኝተው በዚሁ ዋሻ ውስጥ ይታደስባቸዋል። የገፈገፍ ቅድስት ሐና ቤተ ክርስቲያን እጅግ ብዙ ነው ከቤተ ክርስቲያኒቱም ግርጌ የሚገኘው በሏ መካን ስለሚያስወልድ ልጅ የሌላቸው መካኖች ሴቶች ፀበሉን እየጠጡ ልጅ ይወልዳሉ አይጥም ሆነ ሌላ ተባይ የቤተ ምቅደሷን ንዋየ ቅድሳት አይነካም በዚችም በዓል መቅድስ ዓመት እስከ አመት ቅዳሴ ይቀደስባታል። በዚችም ቤተ ክርስቲያን የዓመት በዓል የሚከበረው ቅድስት ሐና በተወለደችብት መስከረም ፲፩ ቀን በአረፈችበት ኅዳር ፲፩ ቀን ነው ።

የዚች ተአምረኛ ታቦት ቤተ ክርስቲያን የምትገኝበት ቦታ ወይና ደጋ ስለሆነ ባቄላና አተር ገብስና ስንዴ ብቻ ነው ።

እንግዲህ ከዚህ በላይ ስለገፈገፍ ሐና ቤተ ክርስቲያን ባጭሩ ገልጸናል የሚቻላችሁ እየሔዳችሁ በመጐብኘት የሀገራችሁን ታሪክ ብታውቁና ብትረዱ መልካም ነው ። በጆሮ የሰሙትን ዜና በዓይን አይቶ መረዳት ያስፈልጋልና ።

አባ ገብረ መስቀል ተሰዬ



www.ethiopianorthodox.org

# የጤና ዓምድ

በመሠረቱ ጤና ለሰው ልጆችና ደመ ነፍስ ላላቸው ፍጥረታት ሁሉ ተፈላጊና መሠረታዊ ሀብት ነው ። በመሆኑም በሕመም መሠቃየትን ማንም የሚፈልግ የለም ለምሣሌ አዕምሮና ልብም ላላቸው የሰው ልጆች ይቅርና ለእንስሳትም እንኳን ጤና ተፈላጊ ነው ቀደም ሲል ማለትም በዘመነ አበው ሁላችንም እንደምናውቀው ከፍተኛውን የሕመም ገፈት ቀማሽ የሆነውን ኢዮብ ብናስታውስ የሕመም ስቃይ ቢበዛበትና እንደአሁኑ ዘመን ለሕመም ማስታገሻ የሚያዘጋጁ ሊቃውንት ባለመኖራቸው ሕመም ስቃይ ቢበዛበት ፡ የሚያደርገው ወይም የሚያድነው ባለማግኘቱ የሚወደውን አምላኩን እንዲፈውሰው ብዙ ጊዜ በጸሎት ጠይቆ የመዳኛው ጊዜ

እንዳልደረሰ ባየ ጊዜ አምላኩን ላለማሳዘን ሲል የተወለድኩባት ቀን የተረገመች ትሁን አለ ። ይህም የሚያመለክተን በሽታ በሰው ላይ ወይም በፍጥረታት ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ እንደሚያደርስ ለመረዳት እንድንችል ነው ። በመሆኑም ኢዮብ የሚያከብረውን አምላኩን በእርሱ ዘመንም ሆነ እስከዓለም ፍጻሜ የማዳን ሥልጣን በእጁ ያለ እግዚአብሔር ባላወቀው ሰዓት ደህንነትን ሰጠው ኢዮብ ተፈወሰ ። በዘመናችን ግን የኢዮብ የመጀመሪያ ፈዋሽ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ዕውቀትን በመስጠቱ ማለትም ለሕክምና ጠበብቶች ግዙፉንና ረቂቅ የሆኑትን የበሽታ ተሕዋስያንን በቀዶ ጥገናና በሌላም ምርመራ በሚሊዮን ሳይሆን በሚሊያርድ የሚቆጠሩ ሕሙማን ማለትም ዳግማዊ ኢዮብ የሆኑት በሽተኞች ተፈውሰዋል ፡ በመዳንም ላይ ናቸው ።

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በዚያው በዘመነ አበው የተደረገውን ደህንነት ለማወቅ ብንፈልግ ንዕማንን እናገኛለን ። ይህም ሰው የሦሪያዊት አለቃና ቆራጥ ጀግና እንደነበር ፡ በመጽሐፈ ነገሥት ላይ እናገኛለን። ነገር ግን ምንም ጀግና ሰው ቢሆንም ጤናው የተቃወሰ ሆነ ፡ ያውም በጊዜው አስቀያሚ በነበረው የለምጽ በሽታ ነው። ሆኖም በመሠረቱ የሰው ልጆች ስለጤንነታቸው ሲሉ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ገንዘብ በማውጣት በዚያን ዘመንም ሆነ በአሁኑ ዘመን ከቅርብ ወደ ሩቅ ለመሄድ ለሕመም ደህንነት መፈለግ የተለመደ ነው ። ንዕማን ከሶርያው ንጉሥ ደብዳቤና አስር መክሊት (ብር ፯ሺህ) ወርቅና አስር መለወጫ ልብሶች አስይዞ ወደ እስራኤል ንጉሥ ሰደደው ። የእሥራኤል ንጉሥም በመጣለት እጅ መንሻ አልተደሰተበትም ። በዘመኑ የነበረው ነቢዩ ኤልሣዕ ግን እግዚአብሔር ያንን ጀግና የላከው ለደህንነት እንጂ ለፖለቲካ አለመሆኑን ባደረበት መንፈስ አውቆ ወደ እርሱ እንዲመጣ ጠየቀው ንዕማንም ወደ ኤልሣዕ መጣ በደጃፉ ፊት ለፊት ቆመ ፡ ኤልሣዕም ንዕማንን ሂድ በዮርዳኖስ ውሃ ሰባት ጊዜ ታጠብ/ሥጋህም ይፈወሳል አንተም ንፁህ ትሆናለህ ብሎ ወደ እርሱ መልዕክት ላከበት ። ንዕማን ግን ተቆጥቶ እንዲህ አለ . . እነሆ ወደኔ የሚመጣ ቆሞም የአምላኩን የእግዞአብሔርን ስም የሚጠራ በእጅ ዳስሶ የሚፈውሰኝ መስሎኝ ነበር የደማስቆ ወንዞች አባናና ፋርፋ ከእስራኤል ወንዞች ሁሉ አይሻሉምን? በእነርሱስ ውስጥ መታጠብና መንፃት አይቻልም ኖሯልን? ብሎ ዞር ብሎ ተቆጥቶ ሄደ ። ባሪያዎቹም ቀርበው ... አባት ሆይ ነቢዩ ታላቅ ነገርስ እንኳን ቢነግርህ ኖሮ ባደረግኸው ነበረ ፡ ይልቁንስ ታጠብና ንፁህ ሁን ቢልህ እንዴት ነዋ? ብለው ነገሩት ። ወረደም የእግዚአብርም ሰው እንደተናገረው በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ ሰባት ጊዜ ብቅ ጥልቅ አለ... ሥጋውም እንደ ገና እንደትንሽ ብላቴና ሥጋ ሆኖ ከዮርዳኖስ ተመለሰ ፡ ተፈወሰ..

ይህ ከላይ የተጠቀሰው የሚያመለክተው እንኳን በቃል ብቻ ተናግረው ሳይንስና ቴክኖሎጂ በፈለሰፋቸው መሣሪያዎች ማለትም በራጅ በላቦራቶሪ ፡ በደም ፡ በሽንት ፡ በሰገራ ምርመራ ተደርጎላቸው እንኳን የማያምኑ ተጠራጣሪ ሰዎች እንዳሉና አንዳንድ ብልህ ሰዎች ወይም ቤተሰቦች መክረዋቸው እንደገና ተረድተው መድኃኒት በቀን ሰባት ጊዜ እንደሚወስዱና በትክክል እንዲታከሙ የሚያመለክት ነው ።

ይሁንና ይህን በዘመነ አበው የተደረገውን በእግዚአብሔርና በነቢያቶች የተፈፀመውን ደህንነት ተመልክተናል ። ከላይ እንደ ጠቀስኩት በዘመናችን እግዚአብሔር በኋላ ዘመን ሳይንስና ቴክኖሎጂ ተስፋፍተው ወይም ተፈላስፈው ካገኙት አንደኛውን ስለተላላፊ የጉበት በሽታ (ኢንፌክሽየስ ሄፒታይተስ) ስለተባለው በመጠኑና በአጭሩ በሰው ልጆች ላይ ስለሚያመጣው ጉዳት እገልጻለሁ። ተላላፊ የጉበት በሽታ (ኢንፌክሺናል ሄፓታይተስ) የበሽታው ምንነት ፡

ተላላፊ የጉበት በሽታ በአገራችን የወፍ በሽታ ተብሎ የሚታወቀው ሲሆን በጣም ጥቃቅን በሆኑ ቫይረስ በተባሉ ሕዋሳት መነሻ የሚከሰትና በተለያዩ ሁኔታዎች ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፍ የጤና ጠንቅ ነው ።

<u>የበሽታው ምልክቶች ፡</u>

፩. ትኩሳት ፡
፪. ከመጠን በላይ የድካም ስሜት ፡
፫. ማቅለሽለሽ ምግብ ማስጠላትና የምግብ ሽታ ማስጠላት
፬. የዓይን ቢጫ መሆን
፭. የሽንት ሻይ መምሰል
፮. በሽተኛው ሲጠናበት አዕምሮን መሳት

<u>የበሽታው መነሻ ፡</u>

ሶስት ዓይነት ሻይ ጠብታውን እንደሚያመጡ ታውቋል እነሱም፡

፩. ሄፕታይተስ ኤ
፪. ,,
፫. ,, ነንኤ ነንቢ (ከሁለቱም የተለዩ ናቸው ከነዚህ ከሶስቱ ዓይነቶች በተለይ በመጀመሪያው የሚያመጣው በሽታ ቀለል ያለ ሲሆን የሚከተለው ሄፕታይተስ ቢ የሚያመጣው በሽታ ከባድ ከመሆኑም በላይ ታማሚው ከታመመ ጀምሮ እስከ ሕይወቱ ዘመኑ ድረስ በሽታውን ሊያስተላልፍ ይችላል።

<u>የበሽታው ማህደር</u>

የበሽታው ማህደርና ምንጩ ራሱ ሰው ሲሆን እንደ ዓይነቱ በዓይነምድር ፡ በሽንት ፡ በደምና በልዩ ልዩ የሰውነት ፈሳሾች አማካይነት ይተላለፋሉ ።

<u>የበሽታው መዛመቻ መንገዶች</u>

እንደባይረሱ ዓይነት የበሽታው መዛመቻ መንገዶች ይለያሉ።

፩.ሄፒታይተስ ኤ :– ኢንፌክሽስ ሄፒታይተስ የሚተላለፈው የበሽተኛው ዓይነ ምድርና – ሽንት በተለያዩ አጋጣሚዎች ወደ ሰው አፍ በሚገቡበት ጊዜ ነው ።

ስለሆነም ፡ የአካባቢ ንፅህና የጐደለበት አካባቢ ፡

– የመጠጥ ውሃ በንጽሕና ባልተያዘበት አካባቢ

– የሽንት ቤቶች በሌሉበትና ኖረውም በሥነ ሥርዓት ጥቅም ላይ በማይጠሉበት አካባቢዎች በብዛት ይከሰታል ።

፪.ሄፕታይተስ ቢ:– ሄፕታይተስ ሲም

እንደተገለፀው በደምና በደም ተረጂዎች አማካይነት ይተላለፋል ። ስለሆነም

– ከታመመና ከዚህ በፊት በበሽታው ተጠቅቶ ከነበረ ሰው ደም ተወስዶ ለሌላ ሰው ሲሰጥ ፡

– በደምብ ያልተቀቀለ መርፌና ሌላም ሰውነትን የሚያቆስል ተግባር በሚደረግበት ጊዜ

– በግብረ ሥጋ ግንኙነት ይተላለፋል ፡

፫. ሄፕታይተስ ኤ ንን ቢ የዚህ መተላለፊያ በውል የታወቀ ባይሆንም በአንድና በሁለት በተገለፁት መንገዶች ሊተላለፍ እንደሚችል ይታመናል ።

<u>ለበሽታው የሚያጋልጡ ሁኔታዎች፡</u>

– በሽታው ዕድሜና ፆታ ሳይለይ በማንኛውም ሰውና በማንኛውም ቦታ ሊይዝ ይችላል ።

– በሽታው ሰዎች በብዛት በሚገኙባቸው አካባቢዎች ፡

በካምፖች ፡
በውህኒ ቤቶች
በትምህርት ቤቶች
በሥፈራ ጣቢያዎች... ወዘተ በብዛት ይከሰታል ።

<u>የበሽታው መተላለፊያ ወቅት ፡</u>

፩.ሄፕታይተስ ኤ የበሽታው ምልክቶች ከመታየታቸው ከብዙ ቀናት በፊት ከ፯ እስከ ፲ ቀን

፪. ሄፕታይተስ ቢ: ከታመመ ጀምሮ እስከ ሕይወት ዘመን

፫. ነን "ኤ " ነን " ቢ:– በውል አይታወቅም

<u>የመከላከል ዘዴ ፡</u>

፩. የአካባቢን ንጽህና መጠበቅ
፪. ውሃን በጤናማ ሁኔታ መጠበቅ
፫.በሽንት ቤት በተገቢው ሁኔታ መጠቀም
፬. መርፌዎችንና የሕክምና መሣሪያዎችን በደምብ መቀቀልና ንጽሕናቸውን መጠበቅ ፡
፭.ሄፒታይተስ – ቢ ይዞት ከነበረ ሰው ደምና የደም እስተዋጽኦዎችን ወስዶ ለሌላ ሰው አለመስጠት ፡
፮. ሄፒታይተስ ቢን በክትባት መከላከል ይቻላል
፯. የግል ንጽህናን መጠበቅ ፡

<u>የበሽታው የመጨረሻ ውጤት</u>

፩. ሄፒታይተስ ኤ አብዛኛው ታማሚ እስፈላጊውን ጥንቃቄ ካደረገ በተለይም ከአልኮል መጠጥ ከተወገደ ፈጽሞ ይድናል አንስተኛው ወደ ክሮኒክ (የሚቆይ) የጉበት በሽታ ይሸጋገራል ።

ወይ. ገጽ ጸሐ ዮሬል





www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ዕረፍት

መምህር አበራ ጥላሁን በጠ ቤተ ክህነት የዕቀድና የጥናት መምሪያ ኃላፊ የነበሩ ሲሆን ከብዙ ጊዜ ጀምሮ አድሮባቸው ከነበረው በሽታ የተነሣ ያረፉትም ነሐሴ ፲፯ ቀን፲፱፻፸፱ ዓ.ም ነው ፤ ወዲያው እንዳረፉ አስከሬናቸው ወደ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተወስዶ ጸሎተ ፍትሐት ሲደረስበት አድሯል ።

ነሐሴ ፲፰ ቀን ፸፱ ዓ.ም ከጧቱ ፫ ሰዓት ከ፴፭ ደቂቃ ላይ አስከሬናቸው ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ለመሔድ ከመሸኘቱ በፊት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ጋር በቅድስ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን በመገኘት ለሚቱ ጸሎት አድርገዋል ፤ እንዲሁም የጠቅላይ ቤተ ክህነት ሠራተኞች አንዳንድ የገዳማትና የአድባራት አስተዳዳሪዎች በርከት ያሉ ካህናት ቁጥራቸው በዛ ያለ ምእመናንና ምእመናት በአሸኛኘቱ ሥነ ሥርዓት ላይ ተገኝተዋል ፤

አስከሬኑ ወደ ደብረ ሊባኖስ ለመሔድ ከመነሣቱ በፊት ሊቀ ብርሃናት ሰሎሞን ገብረ ሥላሴ የቅዱስ ጳውሎስ መ/ት ም/ዲን የሚቹን የሕይወት ታሪክ ለመሸኘት በተሰበሰበው ሰው ፊት አንብበዋል ።

መምህር አበራ ጥላሁን በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ በሞረትና ጅሩ ወረዳ ልዩ ስሙ ጋንማርያም ከተባለው ቦታ ከእናታቸው ከእማሆይ አፀደ ማርያም ማን አለና ከአባታቸው ከመምሬ ጥላሁን አብጥ በ፲፱፻፳፬ ዓ.ም ተወለዱ ፤ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ የአባትና እናታቸውን ቤት ሳይለቁ በተወለዱባት በጋን ማርያም ከመምህር አጣምሬ ፊደል ቆጥረው ንባብና ሰዓታት ዳዊት ተምረው የዲቁና ሥልጣንን በመቀበል በዚያችው በተወለዱባት ጋን ማርያም ቤተ ክርስቲያን በቅዳሴ



መምህር አበራ ጥላሁን

ሲያገለግሉ ቆይተው ከዚያ ወደ ደብረ ብሥራት ዜና ማርቆስ ገዳም በመሔድ ከታወቁት ሊቅ ከአለቃ ጀቤ ረዴ ጾመ ድጓና ምዕራፍ ተመረዋል ፤

፪ኛ ወደ መርሐቤቴ አውራጃ ግራት እግዚአብሔር አብ ሄደው ከታወቁት ሊቅ አለቃ ጥበቡ ዕርገቱ ጾመ ድጓውንና ምዕራፉን ከልሰዋል ።

፫ኛ በ፲፱፻፴፩ ዓ ም ወደ አዲስ አበባ መጥተው ሰዋሰው ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ት ቤት ገብተው ከአለቃ አፈወርቅ ዘውዴ ቅኔ ተምረዋል ፤ እንዲሁም በዚሁ ት ቤት እንዳሉ ከተለያዩ መምህራን ቅዳሴና ዘመናዊ ትምህርት ተምረዋል፡

፬ኛ በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ለከፍተኛ ትምህርት ለ፬ዓመት ወደ ሕንድ ተልከው ፱ ወራት ከተማሩ በኋላ በአየር አለመስማማት ምክንያት ተመልሰው ወደ ሀገራቸው መጥተው ሲያበቁ በ፲፱፻፵፬ ዓ.ም ከተማሪዎች መካከል እንደገና ተመርጠው ለመንፈሳዊ አገልግሎት ወደ ኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳም ተልከው ለ፱ ዓመት ያህል ልዩ ልዩ አገልግሎት ሲሰጡ ኑረው ወደ ሀገራቸው ተመልሰው በወቅቱ በነበሩት ፓትርያርክ መልካም ፈቃድ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የሊቃውንት ጉባኤ አባል በመሆን ፫ ዓመት አገልግለዋል ።

፭ኛ በ፲፱፻፶፯ ዓ ም ወደ ሱዳን ተልከው ካርቱም በሚገኘው የኢትዮጵያ ገዳም መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ለ፮ዓመት አገልግለው ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል ።

፮ኛ በ፲፱፻፷፫ በወሎ ክፍለ ሀገር የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ሆነው ፬ዓመት አገልግለዋል።

፯ኛ በ፲፱፻፷፯ ዓ ም የሰዋሰወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ት ቤት አስተዳዳሪ በመሆን ለ፩ ዓመት አገልግለዋል።

፰ኛ በ፲፱፻፷፰ ዓ ም በጠ ቤተ ክህነት የሥርዓተ ተክሊልና የመንፈሳዊ አገልግሎት ኃላፊ ሆነው ሠርተዋል ፤

፱ኛ በ፲፱፻፷፱ ዓ ም የመንፈሳዊ ፍርድ ቤት ሰብሳቢ ሆነው አገልግለዋል ፤

፲ኛ በ፲፱፻፸፪ ዓ ም እንደገና ወደ ሱዳን ተልከው በካርቱም የመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያንን ለ፪ ዓመት አስተዳድረዋል ፤

፲፩ኛ በ፲፱፻፸፬ ዓ ም ወደ ሀገራቸው ተመልሰው በጠ ቤተ ክህነት የቅርሳቅርስና የቤተ መጻሕፍት ወመዘክር መምሪያ ኃላፊ ሆነው አገልግለዋል ።

፲፪ኛ በ፲፱፻፸፭ ዓ ም የሸዋ ሀ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ሆነው ሠርተዋል ።

፲፫ኛ በ፲፱፻፸፯ ዓ ም የስብከተ ወንጌልና የሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ኃላፊ በመሆን አገልግለዋል ።

፲፬ኛ በ፲፱፻፸፱ ዓ ም ወደ ጥናትና እቅድ መምሪያ ተዛውረው አሁን ከዚህ ዓለም በሞት እስከተለዩበት ዕለት ድረስ ሠርተዋል ።

መምህር አበራ ጥላሁን ፵፯ ዓመት ሙሉ ቤተ ክርስቲያንን በቅን መንፈስ አገልግለዋል ። ከዚህ በላይ የተጻፈው ታሪክ ከተነበበ በኋላ ቅዱስነታቸው አስከሬኑን ለመሸኘት ጸሎተ ቡራኬ ሲያደርጉ ባስተላለፉት ቃለ ምዕዳን "ለፈራሂ እግዚአብሔር ይሤኒ ደኃሪቱ" እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው መጨረሻው ያማረ ይሆናል በሚል ርእስ ተንሥተው ምንጊዜም ቢሆን ሥጋን ከለበሰ ሞት አይቀርም ሞት ለማንም ለማን የማያዳላ ለሁሉም ትክክል የሚደርስ ነው ።

መምህር አበራ ጥላሁን ባለ ዕድሜያቸው ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን ያለዕረፍት በቅንነት ሲያገለግሉ በዛሬው ኑረው ዕለት አርፈው በክብር መሸኘታቸው ከላይ እንደገለጽነው እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው መጨረሻው ያማረ ይሆናል ተብሎ የተነገረው ቃል ትርጉሙን አገኘ ለማለት ይቻላል ካሉ በኋላ ቅድስነታቸው ምክራቸውን በመቀጠል ፤ መታዘዝን ፤ መረዳዳት መጠያየቅ በቁመና ሳሉ ነው በቁመና ሳሉ ሳይረዳዱ ከሞቱ በኋላ ማዘንና ማልቀስ የሚያስገኘው ጥቅም የለውም ፤

ስለዚህ ሁላችሁንም ይህንን ተገንዝባችሁ በቁመና ሳላችሁ እንድትረዳዱ ሁኑ በማለት ቅዱስ ነታቸው ምዕራገ ጸሎት አድርገው ሲያበቁ የሚቹ አስከሬን ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በክብር ተሸኝቷል ።

የዜናው አቅራቢ ቀ. ልሣነ ወርቅ በዛብህ

# ስብከተ ወንጌል ክፍል ፲፩

እያንዳንዱ የወንጌል ሰባኪ ከእውነትና ከድኅነተ ዓለም ለራቀው መልካሙን የምስራች እንዲያበስር ሐላፊነት እንዳለበትና የመሥራትም ሆነ የመናገር ተጠያቂነት ሊኖረው ይገባል ። የክርስቶስም ያዳኝነቱ መልእክት የሆነው የወንጌል ቃል እስከ ዕንፈ ዓለም ድረስ እንዲተላለፍ እንዲዳረስ የፈቀደው በሰዎች አማካኝነት ነው ለዚህ ታላቅ ተግባር የተመረጡ ሁሉ በሕይወታቸውና በአገልግሎታቸው የጌታቸውንና የመድኃኒታቸውን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ማመስገንና ቃሉንም ተዘዋውረው መስበክ ይፈለግባቸዋል ።

ይህን በተመለከተ እስከ 18ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ በዚህ በ፪፻ ዘመናት የስብከተ ወንጌል ሥራ እንደደረቀ ዛፍ ለሕዝብ ፍሬ ሳይሰጥና ጣዕሙ ሳይታወቅ ቦታውንም ሌሎች ነገሮች እንደወረሱት አንዳንድ የታሪክ መረጃ እንዳቀረብን ይታወሳል። በዛሬው ጽሑፋችን ደግሞ በ፲፱ኛው ክፍለ ዘመን እና በ፳ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በየጊዜው የተፈጸመውን የስብከተ ወንጌል ሁኔታ እናብራራለን ።

በተለይም የሃይማኖት ክርክር በአዋጅ ስለቆመ በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ቤተ ክርስቲያን ሰላምና እረፍት አገኘች ሊቃውንቱም ወደተረሱት ምእመናን ዘንድ እየሄዱ ወንጌልን ያስተምሩ ጀመር ልዩ ልዩ ሚሲዮናውያንም በብዛት መግባት የጀመሩት ትምህርት ቤትም የከፈቱት በዚሁ ዘመን ነው ። ሚሲዮናውያን ገብተው እንዲያስተምሩ ቢፈቀድላቸውም የራሳቸውን መንጋ ከማስተማር በቀር የሌላውን እንዳይነጥቁ የተጠመቀውን ሁለተኛ እንዳያጠምቁ በጠቅላላው ኢትዮጵያ የወንጌል ስብከት ችግር የሌለባት ስለሆነች በህክምና ፤ በርሻ ፤ በልዩ ልዩ ጥበብ ሕዝቡን እንዲረዱ ከመምከራቸውም ሌላ "አመልህን በጉያህ ስንቅህን ባህያህ" የሚል ጠቅለል ያለ መመሪያ ስለሠጡ ሁሉም በሰላም ይኖር ጀመር ።

በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የስብከተ ወንጌልን ሥራ ያስፋፉ ጀመር ። ነገር ግን የትምህርቱ አሠጣጥ ከአሁኑ ዘመን ለየት ያለ ነበር ። የየደብሩ አለቆች በየማምንቱ እሁድ በክብረ በአል ጊዜ በየቤተ ክርስቲያኑ አውደ ምህረት ምንጣፍ አስነጥፈው የአንድ ምታ ትርጓሜን ያስተምሩ ነበር ።

በዓቢይ ጾም ከቅኔ ማህሌት እየተገኙ ወንጌል ይተረጉሙ ነበር ፤ በሕማማት ደግሞ ሊሰግዱ ለተሠበሰቡት ምእመናን የትምህርተ ኅቡአትን እና የኪዳንን ትርጉም በተራ ያካሄዳሉ በጾመ ፍል





www.ethiopianorthodox.org

ስታ ደግሞ የውዳሴ ማርያምና የቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ ሊያስቀ ድሱ ለተሰበሰቡት ምእመናን ያስ ተምራሉ ዳግማዊ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱም በግቢ ኪዳን ምህረት እየተገኙ በሕማማት እና በጾመ ፍልሰታ ከላይ የተጠቀሱትን ትም ህርቶች ከሊቃውንቱ ያዳምጡ ነበር ሊቃውንቱም ሲያስተምሩ በጉባኤ እንዳጠኑት አድርገው ያስ ተምሩ ነበር እንጂ አሻሽለው እያ ስተምሩም ነበር ይህም ከጥንት መምህራን ሲወርድ ሲዋረድ የመ ጣውን ዘዴ ተከትለው ነበር ። የሚያስተምሩት ።

ይሁን እንጂ በዚያን ዘመን የነ በሩት ሊቃውንት ወንጌል ለመስ በክ የተፋጠኑ ቢሆኑም የመጽ ሐፍ ውድነት ስለነበር በእነሡም በምእመናንም ዘንድ ታላቅ ችግር ነበር ለመጀመሪያ ጊዜ አባ ሮሚ ዘአድያመ ዋድላ መጽሐፍ ቅዱ ስን ከግእዝ ወደ አማርኛ ተረ ጐሙ ። አራቱ ወንጌላት በ፲፰፻፲፯ ዓ ም ሲታተሙ ሙሉ አዲስ ኪዳን ግን በ፲፰፻፴፪ ዓ ም ታተመ ጠቅላላ መጽሐፍ ቅዱስ ግን በ፲፰፻፵፫ ዓ ም ታትሞ ወጥቷል። ይህ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ የታተ መው በለንደን መጽሐፍ ቅዱስ ማተሚያ ቤት ነው ። ቶማስ ፒል የተባለ እንግሊዛዊ በእርማት እረ ድቶአቸዋል መጽሐፍ ቅዱስ በአ ማርኛ ቢታተምም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃ ውንቱም ምእመናኑም ሳይጠቀ ሙበት ለብዙ ጊዜ ቆየ ።

ሁለተኛው አባ አረጋዊ የተ ባሉ መነኩሴ በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በ፲፰፻፸፰ ዓ/ም ፍላድ የተባለው እንግሊዛዊ እየረ ዳቸው ሁለተኛ ጊዜ ሙሉ የአማ ርኛ መጽሐፍ ቅዱስ አሳተሙ ብዙ የመጽሐፍ እትም በመግባቱ ስብከተ ወንጌል ይስፋፋል የሰባክ ያን ብዛት ይኖራል የትምህርቱም ዘዴ ይሻሻላል ተብሎ እምነት ተጥሎበት ነበር ። ነገር ግን እንደ ታሰበው ሳይሆን አንዳንድ ብል ሆች ሲጠቀሙበት አብዛኛዎቹ አልተጠቀሙበትም ስብከተ ወን ጌል እንዲስፋፋ ቤተ ክርስቲያን እድገት እንድታገኝ መጽሐፍ ቅዱስን ካህናቱም ሆኑ ምመናኑ እንዲለማመዱት ለማድረግ ዳግ ማዊ ምኒልክ ለንደን ወደሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ተላል ከው አራቱ ወንጌሎችንና ግብረ ሐዋርያትን በግእዝና በአማርኛ አባዝተው እንዲልኩላቸው ተነጋ ገሩ ። የተጠየቀውም መጽሐፍ በብዛት ታትሞ መጣ ይህም ለስብ ከተ ወንጌል ታላቅ መስፋፋትን አድርጓል።

ቀጥሎ በ፲፱፻፲፯ ዓ ም ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወ ሥላሴ አራቱን ወን ጌሎችና ግብረ ሐዋርያትን በግዕ ዝና በአማርኛ አዘጋጅተው ብርሃ ንና ሰላም ማተሚያ ቤት እንዲታ ተም በማድረጋቸው የመጽሐፍ ችግር በመጠኑም ቢሆን ስለተቃ ለለ ሰባክያንም ሆኑ አንባብያን ከመጽሐፍ ጋር የመተዋወቅ ልምድ እያገኙ ሄዱ ይኸው ሥራ ቀጥሎ ሊቃውንቱ ጠቅላላ መጽ ሐፍ ቅዱስ በግእዝና በአማርኛ አዘጋጅተው በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት እንዲታተም ካቀ ረቡ በኋላ በ፲፱፻፳፰ ዓ ም ጠላት በመግባቱ ሳይታተም ቀረ። ይህ ሁኔታ ለስብከተ ወንጌል መዳከ ምና አለመሻሻል እንቅፋት ሆኖ ቆይቷል ።

በወንጌል ሰባክያን የነበረው የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ጥንታዊ ነቱን ባለመልቀቅ በሰባክያን ጐላ ያሉ ድክመቶች ይታዩባቸው ነበር። ጥቂቶቹን ብንጠቅስ ፩ኛ ርእስ መልቀቅ ይህም ማለት የጀ መሩበትን ርእስ ትተው ወደ ሌላ ጉዳይ መግባትና በዘፈቀደ መና ገር ፪ኛ/ ቋንቋው ይህም ማለት ምእመናኑ የሚናገሩበት ቋንቋ አማርኛ ሆኖ ሳለ ሰባክያን ግን አብዛኛውን ጥቅስና ጠቃሚ የወን ጌል ትምህርት በግእዝ በማስተማ ራቸው ፫ኛ/ ምዕራፉንና ቁጥሩን በሚገባ ለይተው ለምእመናኑ ሳይ ናግሩ መጽሐፍ እንዲህ ይላል ከማ ለት በቀር ምዕራፍና ቁጥር ለይ ተው ባለመጥቀሳቸው ሕዝቡን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋራ ሊያቀራር ቡትና ሊያስተዋውቁት አልቻ ሉም ነበር ።

<u>ለምሳሌ</u> የገነተ ጽጌ ጊዮርጊስ አለቃ የነበሩት መልአከ ገነት ተድላ ኋላም እጨጌ ሳዊሮስ የተባ ሉት ከዕለታት አንድ ቀን ንግ ሥት ዘውዲቱ ከመኳንንቶቻቸው ጋር በተገኙበት ሊቃውንቱና ካህ ናቱ ባሉበት ምዕራፍና ቁጥር እየ ጠቀሱ ቁመው ጥሩ ዘመናዊ ስብ ከት ሰበኩ ይባላል። በስብከታ ቸው ንግሥቲቱና ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ጠርተው አመስገ ኑአቸው ወደፊትም በዚህ ዓይነት እንዲሰብኩ ነግሯአቸው ውጭ አገር ተምረው የመጡት መምህራ ንም ስብከት ዛሬ ገና ሰማን እያሉ አደነቁ ሊቃውንቱና ካህናቱ ግን የስብከቱ አሰጣጥ ለወጥ ስላለባ ቸው ትችት አቀረቡ ይህም የስብ ከት ዘዴንና ብልሀትን ካለማወቅ የተነሣ ሳይሆን አይቀርም በዚህ ዘመን የነበሩት ሰባክያን በልማድ እንጂ ከላይ የተሰበከውን ስብከት አስመስለው መስበክ አቅቶአ ቸው አይደለም ። ይኸውም ከውጭ ለስብከት የሚረዱ በርከት



# በጠ/ቤተ ክህነት ለሰባክያነ ወንጌል ኮርስ ተደረገ

ያሉ መጻሕፍት ይገቡ ነበር በሀገ ራችንም ማተሚያ ቤት ስለተቋ ቋመ ጉሐ ጽባሕ ጥሩ ምንጭ እነዚህን የመሣሰሉት መጻሕፍት ይታተሙ ስለነበር ችግር አልነበ ረም ችግሩ ሊቃውንት ወደእነዚህ መጻሕፍት ትኩረት አለማድረጋ ቸው ነው መማር ለማስተማር ከሆነ ማንኛውም የወንጌል አስተ ማሪ ሁሉ ለማስተማር ከመሄዱ በፊት ለማስተማር የሚጠቅሙ ትን መጽሐፍት ማንበብና መዘጋ ጀት ይፈለግበታል ። ይህን ካደረገ በትምህርቱ ሰዎችን ሊጠቅም ይችላል ። የራቁትን ያቀርባል የተበሳጩትን ወደ ደስታ ይመል ሳል ። የወንጌል መምህራን ይህን የመሰለውን ሁኔታ አሚልተው ከተገኙ የተሰጣቸው ሐላፊነት በተግባር እንደተረጐሙት ይቆጠ ራል <u>ለምሳሌ</u> አንድ እረኛ መል ካም እረኛ የሚባለው በጐቹን ጠዋት ከጋጥ አውጥቶ ማታም ወደ ጋጥ ስላስገባ ብቻ አይደለም ለምለም ሳር ጥሩ ውሃ ወደሚገኝ በት አሰማርቶ አውሬ እንዳይበላ ቸው ጠብቆና ተቆጣጥሮ የሰ ቡጐች መሆናቸውን እንዲያውቃ ቸውና እነሱም እንዲያውቁት ያደ ረግ እንደሆነ ነው ።

አንድ የወንጌል አስተማሪም ምእ መናን እንዲበዙና እንዲበረክቱ ቤተ ክርስቲያን እድገት እንድታገኝ ወን ጌል እንዲስፋፋ የምእመናን አንድ ነት እንዲጸና ያደረገ እንደሆነ ነው ወንድሞች በኅብረት ቢኖሩ እነሆ መልካም ነው ። እነሆም ያማረ ነው ተብሏልና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ህዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልኮ መም ሪያ ለሰባክያነ ወንጌል የሞያ ማሻ ሻያ ኮርስ ያደረገው ከመስከረም ፳ ፲፱፻፹ ዓ/ም እስከ ጥቅምት ፳ ቀን ፲፱፻፹ ዓ/ም ነበር ።

በዚህም ኮርስ ላይ ተካፋይ የሆ ኑት ሠራተኞች ፰ ሲሆኑ ከመካከላ ቸው ለአስተማሪነት ጭምር የተ መደቡ ይገኛሉ በኮርሱም ላይ ለመጽሔቶችና ለጋዜጦች ዝግ ጅት ለሥነ ጽሑፍ ፡ ለስብከተ ወንጌል አቀራረብ የሚረዱ ትምህ ርቶች ተሰጥተዋል ።

በኰርሱም መደምደሚያ ቀን የመምሪያው ሐላፊ ሊቀ ካህናት



ሠልጣኞቹ በኮርሱ ላይ

ብርሃኑ ገብረ አማኑኤል ስለኮርሱ አፈጻጸምና ይዞታ የተጠናቀረ ሪፖርት አንብበው ሲፈጽሙ ከኮ ርሱ ተሳታፊዎች የተፈቀደላቸው ሦስት ሊቃውንት ቅኔ አበርክተ ዋል ። ከተበረከቱትም ቅኔዎች ለማስረጃ ያህል ቀጥለን እናቀርባ ለን።

ከቀሲስ ልሣነ ወርቅ በዛብህ

፩ኛ <u>ጉባኤ ቃና</u>

ፍኖተ ይኩን ተክለ ሃይማኖት ዕድሜከ

ከመ ንርከብ ንሕነ ዘተመነይነ ጸጋከ ፡

<u>ትርጉሙ</u> ብፁዕ ወቅዱስ አባታ ችን ተክለ ሃይማኖት ሆይ !

ዕድሜህ ቢሄዱት እንደማያ ልቅ መንገድ ይርዘምልን ።

እኛ ልጆችህ የምንመኘውን ስጦታህን ለማግኘት እንችል ዘንድ

<u>፪ኛ ጉባኤ ቃና</u>

ኢንትአቀፍ ምንተ ሰባክያን ጽድቅ ኩልነ ፡

ተክለሃይማኖት ማህቶት አም ጣነ ያበርህ ለነ ፡

ተርጓሚው የወንጌል ሰባኪ ዎች የሆን ሁሉ ምንም እንሰነካከ ልም መብራት ተክለ ሃይማኖት ያበራልናልና ፡

<u>መወድስ ቅኔ</u>



www.ethiopianorthodox.org

አንሰልው ዮም እስከ አድያ ሚሃ
ለኢትዮጵያ ምድርነ ምሁራነ
መንጌል ካህናት ፤
እንዘ ቦ ብርሃን ተክለሃይማኖት
ሰማዕት
ወተርኅወ በጊዜነ ፤ ዘተአጽወ
ኆኅተ ዚኦሃ ለኤዶም ስብከት ፤
አምጣነ ተፀንሰ ወተወልደ ተክለ
አብ ቃል እምድንግለ ሙሴ ሀብተ
ሚመት
ለዓለም
ፍኖትሂ እንተ ጽድቅ ተክለ ሃይማ
ኖት ፤
ኀበ ዘሠመርነ ስመ ክብር አብጽ
ሐነ በቅጽበት
መወዋዕሊሁ ፀሐይ ዘኢይቀርቦ
ጽልመት ፤
ኮነ ምርኩቦሙ ለዘኖሙ ሊቃው
ንት ፤
ትርጓሜው
ወንጌልን የተማራችሁ ካህናት
ሆይ ! የእውነት ምስክር ተክለሃይ
ማኖት ብርሃን ስላላችሁ የምድራ
ችን ዳርቻ ሁሉ ዞራችሁ አስተ
ምሩ ። በዘመናችንም ተዘግቶ የነበ
ረው የስብከተ ወንጌል ገነት
ደጃፍ ተከፈተ ፤ ተክለሃይማኖት
ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ከሙሴ
ድንግል የሹመት ሀብት ተፀንሶ
ቷውልዷልና ፤
የለዓለሙ ትርጓሜ
የእውነት መንገድ ብፁዕ ወቅዱስ
አቡነ ተክለሃይማኖት ወደፈለግ
ነው የክብር ስም በፍጥነት አደረ
ሰን ፤
ጨለማ የማይቀርበው ፀሐይ ዘመ
ኑም ተኝተው የነበሩ ሊቃውንት
ተነሥተው ወደ ሥራ የሚሠማሩ
በት ሆነ ማለት ነው ።
ከዚያ በኋላ በብፁዕ አቡነ ዜና
ማርቆስ የቅዱስ ፓትርያርኩ
ረዳት ሊቀ ጳጳስ ጸሎተ ቡራኬ
የኮርሱ ፍጻሜ ሆኗል ።
እንዲሁም ከጥቅምት ፯ እስከ ፲፩
ቀን ፲፱፻፹ ዓ ም ድረስ የመንበረ
ፓትርያርክ አጠቃላይ የሰበካ መ
ንባኤ የተደረገ መሆኑ ታውቋል

## የጤና ዓምድ

(ከገጽ ፲፯ የዞረ)

በሽታው ጠንቶበት ይሞታል በተ
ለይ በሽታው በነፍሰጡሮች ላይ
ይከፋል ።

፪. ሂፒታይተስ ቢ. ብዙው
ታማሚ ቢድንም ይህ በሽታ ወደ
ክሮኒክና የጉበት መበላሸት ሲሮ
ስስ የሚያደርስ ነው ።

፫. ሂፒታይተስ ነን ኤ ነን ቢ.
– በአብዛኛው ሁኔታ ይከሠታል
ቋሚ ሕክምና የለውም ነገር
ግን ሊደረጉ የሚገባቸውን ቀጥ
ለን እንጽፋለን ሂፒታይተስ ኤ.
ክትባት ወዲያው የሚሰጥ ነው
ሂፒታይተስ ቢ. ደም የሚሰጡትን
ሰዎች መምረጥ ለወደፊቱ እንዳ
ይገዘ ክትባት መስጠት ሂፒታይ
ተስ ቢ. ክትባት በወር ፤ በሶስት
ወርና ፤ በስድስት ወር የሚሰጥ
ነው።

ተገቢ ዕረፍት መውሰድ ፈሳሽ
ነገር በብዛት መስጠት ቫይታሚን
ቢ. እንዲሁም ጣፋጭ ምግቦችን
እንዲወስድ ማድረግ ቅባት ነክ
ነገሮችን መስጠት ክልክል ነው ።
ፕሬዲን ሶለን መድኃኒት መስ
ጠት ግሉኮስ 5% መስጠት ዲ.ሡ.
4% ቫይታሚን ቢ. ኮምፕሌክስ
መስጠት ተገቢ ነው ፤ ከዚህ በላይ
አሳሳቢ ከሆነ ግን ወደ ሆስፒታል
መላክ ነው።

አቅራቢ አባ ይትባረክ ዓለሙ

## ማረሚያ

በትንሣኤ መጽሔት ቁጥር ፷፲፱ ጥቅምት ፲፱፻፹ ዓ ም የቤተሰብእ
ዓምድ በሚለው ርእስ ገጽ ፳፩ ላይ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ
ሃይማኖት፦ቃለ ምዕዳንና አባታዊ ምክር አደረጉ የሚለው ስሕተት
ስለሆነ ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ቃለ ምዕዳን አረጉ ተብሎ ይነበብ ።



# የዙር አባ አረጋዊ ገዳም ታሪክ በአጭሩ

ዙር አባ ጽርሐ አረያም የሚል
የክብር ስም አላት የምትገኘውም
በጎንደር ሀ/ስብከት በጋይንት
አውራጃ ላይ ጋይንት ወረዳ ነው
ገዳሚ የተመሠረተችው በስድስተ
ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዓፄ ገብረ
መስቀል ዘመነ መንግሥት ነው
ቅዱስ ያሬድ ከብሉይና ከሐዲስ
የተቀመመውን ጣዕመ ዜማ የደረ
ሰው በዚሁ ዘመን መሆኑን ከታ
ሪክ እንረዳለን ።
ንጉሡ ዓፄ ገብረ መስቀል የቅ
ዱስ ያሬድን ጣዕመ ዜማ ሲያዳ
ምጥ ልቡ ከጣዕመ ዜማው የተነሣ
ተመስጦ በአንካሴው እግሩን እን
ደወጋውና ደሙም ከደመ ሰማዕ
ታት እንደተቆጠረለት ይነገራል።
ቅዱስ ያሬድ ከአቡነ አረጋዊ
ጋር ለመገናኘት ወደ ደብረ ዳሞ
ሂዶ ተገናኝቷቸዋል በደብረ ዳሞ
አብረው ለጥቂት ቀናት ከሰነበቱ
በኋላ ከንጉሡ ዓፄ ገብረ መስቀል
ጋር በመሆን ወደ ጣና ባሕር
ተጓዙ በዚያም ቅዱስ ያሬድና አፄ
ገብረ መስቀል ሲሰነብቱ አቡነ
አረጋዊ ወደ ዙር አምባ ተጉዘው
ከተራራው እግር ደረሱ ወደተራ
ራው ራስ ለመውጣት አስበው
መውጫ በማጣታቸው ሲጨነቁና
ወደፈጣሪም ሲጸልዩ ሰነበቱ ፤
በሦስተኛው ሱባኤ መልአኩ
ቅዱስ ራጉኤል ወደእርሳቸው
መጥቶ ዙር አባ መንገለ ምሥራቅ
ለደብር አባ ሆይ! በተራራዋ ወደ
ምሥራቅ በኩል ዙር መውጫ
ታገኛለህ ስላላቸው በምሥራቅ
በኩል ዙረው ነጭ ሀረግ በመያዝ
ወደ ተራራው ራስ ለመውጣት
ችለዋል ከዚያ ወዲህ ቦታዋ ዙር
አባ ተብላለች ።
አቡነ አረጋዊ ከተራራው ላይ
ከወጡ በኋላ ቦታው ስላስደሰታ
ቸው ለዚህ ቦታ ጽርሐ ዓርያም
እንጅ ሌላ ተመሳሳይ ቦታ ሊገኝ
ለት አይችልም ብለው ስለተናገሩ
ጽርሐ አርያም ተብሎ ተሠየመ
ይባላል ዓፄ ገብረመስቀል ቤተ
ክርስቲያኑን እያሠሩ ከተራራው
ሥር ቤት አሰርተው ሦሥት
ዓመት ያህል ኑረዋል የኖሩበትም
ቦታ ዓጼ ከተማ እየተባለ እስከዛሬ
ይጠራል እንዲሁም ባለቤታቸው
እቴጌይቱ ተቀምጠውበት በነበ
ረው ቦታ አጠገብ በዚያን ዘመን
ውኃ ፈልቆ ስለነበርና አሁንም
ውሃው ሳይደርቅ ስለሚገኝ እቴጌ
ውሃ እየተባለ ሲጠራ ኑሯል አሁን
ግን ከዘመን ብዛት የተነሣ ንግግር
እየተለዋወጠ እቴ ውሃ ይባላል ።
አቡነ አረጋዊ ሕገ ወንጌልን
እያስተማሩ ፫ ዓመት በዚሁ ቦታ
ኑረዋል ቅዱስ ያሬድም በአክሱም
ጽዮን የደረሰውን ጸዋትወ ዜማ
ከማስተማሩ ሌላ ለጌታችን ለመ
ድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ
ሥጋና ደም የሚጸለየውን ዝማሬ
በ፳ ክፍሎ የዘመረው በዚሁ ደብር
ነው እነርሱም ፤

| | |
|---|---|
| ፩ ዝማሬ | ፬ አኰቴት |
| ፪ ጽዋዕ | ፭ ምሥጢር ናቸው |
| ፫ መንፈስ | |

በተጨማሪም ሰባት ጊዜ ተመ
ላልሶ የሚጸለየውን መዋሥዕት
ከዚሁ ቦታ ደርሷል ሰባት ጊዜ
ተመላልሶ መጸለዩም ስለ ፬ ባሕር
ያተ ሥጋና ስለ ባሕርያተ ነፍስ
ሲሆን ፀዓተ ነፍስን ርደተ መቃብ
ርን ርደተ ገሃነምን ትንሣኤ ዘጉባ
ኤን በዊም መንግሥተ ሰማያትን
ቀዊም በየማንን ቀዊም በጸጋምን
እያሰቡ የሚጸልይ ነው ፤
ይህ የቅዱስ ያሬድ የመጨረሻ
ድርሰት የተደረሰበት ቦታ ከአም
ባው ላይ ከቤተ ክርስቲያኑ በስተ
ምሥራቅ ከጥቁር እንጨት ሥር
ሲሆን ይህም እንጨት እስካሁን
ድረስ መሀል ለመሀል ከሁለት
የተሰነጠቀ ሆኖ ግማሽ ጉኑ ደረቅ
ግማሽ ጉኑ ልምላሜ ያለው ሆኖ
ይገኛል ፤
ዓጼ ገብረ መስቀል ቤተ ክርስ
ቲያኗን አሠርቶ ከፈጸመ በኋላ
ዙር አባ ጽርሐ አርያም እንደ ቤተ
መንግሥታችን እንደ አክሱም
ጽዮን እንደ ቤተ ጸሎታችን እንደ
ደብረ ዳሞ ትሁን ብሎ አውጀል
ቅዳሴ ቤቱንም አክበረው ዓጼ
ገብረመስቀል ወደቤተ መንግ
ሥቱ ወደ አክሱም አቡነ አረጋዊ
ወደ ደብረ ዳሞ ተመልሰዋል
ቅዱስ ያሬድም ወደ አክሱም
ሲሄድ ስሜን ደብረ ሐዊ ቀር
ቷል።
እመቤታችን ድንግል ማርያ
ምም በስደት ጊዜ ከልጇ ከኢየሱስ
ክርስቶስ ጋር የጣናን ባሕር ከጐበ
ኙች በኋላ ገሊላ ከተባለው የተ
ራራ ጫፍ ላይ እንዳረፈች ይነገ
ራል ።
ታሪኩ የሚገኘው ከድርሳነ
ኡራኤል ነው
ከቅዱስ ያሬድ ከ፮ኛው መቶ
ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ
በዙር አባ ጽርሐ አርያም ገዳም
በዝማሬ መዋሥዕት መምህርነት
ተሹመው ከእየ አህጉረ ስብከቱ
ተምረው ለማስመረቅ ለሚመጡ
ደቀ መዛሙርት የመምህርነት
ማዕርግ የሰጡ መምህራን ብዛት
፵፬ ናቸው ።

የዜናው አቅራቢ
መሪጌታ መልኬ ዓለሜ



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሊቃውንት

**<u>የሊቀ ጠበብት</u>**
**<u>ሐረገ ወይን ደምሴ</u>**
**<u>አጭር የሕይወት ታሪክ</u>**

ሊቀ ጠበብት ሐረገ ወይን ደምሴ ከመምሬ ደምሴ ተ/አረጋዊና ከወ/ሮ ወለተ መድኅን መርሻ በይፋትና ጥሙጋ አውራጃ በማፋድ ወረዳ ልዩ ስሙ ሴራ ጨለንቆ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በተባለው ሰበካ ውስጥ በ፲፱፻፳፭ ዓ/ም ተወለዱ ።

ዕድሚያቸው ለትምህርት እንደደረሰ በዚሁ አውራጃና ወረዳ ወደሚገኘው ዓቃቢት ቅዱስ ሚካኤል ደብር በወላጆቻቸው አማካይነት ተወስደው አባ ወልደ ሐና ከተባሉት መምህር ስአታት በቃል አጥንተዋል ።

ከዚያም ወደ ተጉለትና ቡልጋ አውራጃ ናስ ማርያም በተባለው ደብር ሄደው ከአለቃ ቤተ ማርያም ጸመ ድጓና ምዕራፍ ተምረዋል።

ሊቀ ጠበብት ሐረገ ወይን ደምሴ ከፍተኛ ትምህርታቸውን በ፲፱፻፴፫ ዓ ም ወደ አዲስ አበባ መጥተው በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት

፩. ከመልአከ ገነት ጥሩነህ አቋቋም ዝማሬና መዋስዕት በሚገባ ተምረዋል ።
፪. ከመ/ጋቢ ምስጢር ጌራወርቅ ቅኔ ተምረዋል ።
፫. ከመ/ጋቢ ብሉይ መዘምር ታዬ ትርጓሜ መጻሕፍት አጥኝተዋል።
፬. ከመምህር ወርቅነህ ኃይሌ በአሁኑ ጊዜ የመታሰቢያ ቤቱ ምክትል ሊቀ ሊቃውንትና ከአባ መንግሥቱ መዝገብ ቅዳሴ በሚገባ ተምረዋል። ለዚህም ችሎታው መለኪያ ይሆን ዘንድ በዲፕሎማ ተመርቀዋል ።

ሊቀ ጠበብት ሐረገ ወይን ደምሴ ባላቸው ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤተ ክርስቲያንንና ምዕመናንን ለማገልገል ወደ ሥራ ዓለም ለመግባት ራሳቸውን ከአዘጋጁ በኋላ ።

፩ኛ/ በይፋትና ጥሙጋ አውራጃ የሸንኮሮን ማርያምን ደብር

፪ኛ/ የወይን ውሃ ቅዱስ ገብርኤልን ደብር በአስተማሪነት ተልከው አቋቋም ቅዳሴና መጽሐፍ ቅዱስ በማስተማር ሰፊ መንፈሳዊ አገልግሎት ፈጽመዋል ።

ከዚህም በኋላ በኢትዮጵያ መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ ቤት በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ በታህሣሥ ወር ፲፱፻፷፫ ዓ ም ተዘዋዋሪ ሰባኬ ወንጌልና የራድዮ ፕሮግራም መዝሙር አዘጋጅ ሆነው ተመድበው በመሥራት ቅን አገልግሎት ሰጥተዋል ። በተለይ በአቋቋም ትምህርት ባላቸው ችሎታና መልካም ድምፅ ልዩ ልዩ ዜማዎችንና መዝሙሮችን በካሴት በማስቀረጽ ለቤተ ክርስቲያን ቅርስ አትርፈዋል በዚሁ የስብከተ ወንጌል መምሪያ ለጥቂት ዓመታት ከሠሩ በኋላ በመካከል ወደ ይፋትና ጥሙጋ አውራጃ ተዛውረው የአውራጃው የስብከተ ውንጌል መምህር በመሆን በየወረዳው እየተዘዋወሩ የወንጌልን መልእክት ከማዳረሳቸውም በላይ ሕዝቡን በማስተባበር ብዙ የፈራረሱ አብያተ ክርስቲያናትን እንዲታደሱ አድርገዋል ።

እንደገናም ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው ከላይ በተጠቀሰው መምሪያ ቋሚ ሥራቸውን በመቀጠል ብዙ የሥራ ውጤት ከማሳየታቸውም በላይ በትርፍ ጊዜአቸው ፩ኛ በአዲስ አበባ መካነ ሕይወት ገብረ መንፈስ ቅዱስ ፪ኛ በደብረ ገሊላ አማኑኤል አብያተ ክርስቲያናት በተለያዩ ዓመታት በመዘምርነት አገልግለዋል ።

ለረጅም ጊዜ የሰጡት መንፈሳዊ አገልግሎትና ሙያቸው ለታላቅ ማዕርግ የሚያበቃቸው ሆኖ በመገኘቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በ፲፱፻፸፯ ዓ ም የሊቀ ጠበብትነት ማዕርግ ሰጥተዋቸዋል ።

ሊቀ ጠበብት ሐረገ ወይን ደምሴ በሕፃንነት ዕድሚያቸው የዓይን ስውርነት አደጋ ስለደረሰባቸው ይኸንን ሁሉ መንፈሳዊ ትምህርት የተማሩት በጽሑፍ በመደገፍ ሳይሆን በቃል በማጥናት ነበር ።

ሊቀ ጠበብት ሐረገ ወይን ደምሴ እግዚአብሔር በተፈጥሮ ጸጋ የሰጣቸውን መልካም ድምፅ እና ላሀይ በተግባር የሚያውሉ ማኅሌታይ ስለነበሩ እሳቸው ያሉበት ማኅሌት ልዩ ድምቀትና ውበት እንደነበረው ሁሉም የሚያውቀው ነበር ።

ሊቀ ጠበብት ሐረገ ወይን ደምሴ በሙያቸው የተመሰገኑ በጠባያቸው የተወደዱ ቁም ነገረኛ ትልቁንም ትንሹንም አክባሪና ፍጹም ወንድም ወዳጅ የነበሩ ሲሆኑ በሥጋ ወደሙ በመወሰን ተዘጋጅተው ወደ ፈጣሪያቸው

ወደ ገጽ ፫ ዞሯል





# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ስምንት ብር በማስከፈል ይሰጣል ።
ለዚሁ ጥያቄ ቢሮርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፡

የስልክ ቁ.
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org